# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለገላትያ ሰዎች የጻፈው መልእክት

## መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈበት ዘመን በ48 እና በ50 ዓ.ም. መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። መልእክቱ የተጻፈው በተለይ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፥በገላትያ ክፍለ ሀገር ውስጥ በየሥፍራው ለሚገኙ ማኅበረ ምዕመናን ሁሉ ነው። በዚያን ዘመን፥አንዳንድ 'ክርስቲያኖች ነን' የሚሉ ሐሰተኞች የአይሁድ መምህራን ተነሥተው፥ ክርስቲያኖች የአይሁድን ሃይማኖት ሥርዓት መፈጸም፥የኦሪትን ሕግ መጠበቅ ይገባቸዋል' እያሉ በየቤተ ክርስቲያኑ ሰርገው እየገቡ ያስተምሩ ነበር። በዚህም ትምህርታቸው ማኅበረ ምዕመናኑን በክለው ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስም ሐሰተኞቹን መምህራን በነገር እየኰነነ፥እንዲህ ያለው ትምህርት ከክርስቶስ ወንጌል ጋር የሚቃረን መሆኑን በማስረዳት፥ከኃጢአት ባርነት ነፃ መሆን የሚቻለው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ መሆኑን ለገላትያ ሰዎች ግልጥልጥ አድርጎ ያሳያቸዋል።

---

## ምዕራፍ 1

1-2 ከሐዋርያው ጳውሎስና አብረውት
ካሉ ክርስቲያኖች፥ለገላትያ አብያተ ክርስቲ
ያን የተላከ። የእኔ ሐዋርያነት ከሰው ሳይ
ሆን፥ በቀጥታ ከኢየሱስ ክርስቶስና፥ከሞት
ካስነሣው ከእግዚአብሔር አብ ጥሪ፥ የመ
ነጨ ነው። 3 የእግዚአብሔር አብና የጌታ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእና
ንተ ይሁን። 4 እንደ አምላካችንና እንደ አባ
ታችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ፥ከምንኖ
ርባት ከዚች ክፉ ዓለም ሊያድነን ክርስቶስ
ስለ ኃጢአታችን ሞቶልናል። 5 ይህን ያደረ
ገልን አምላክ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር
ምስጋና ይግባው፤አሜን።
6 በክርስቶስ የዘላለምን ሕይወት እንድታ
ገኙ፥በፍቅሩና በጸጋው የጠራችሁን አምላክ
ትታችሁ፥ ከመቼው ሌላ ወንጌል ተከትላ
ችሁ ነኰዳችሁ? ይደንቀኛል! ወደ መንግ
ሥተ ሰማይ የሚያደርሰው መንገድ፥ ይህ
መስሏችሁ ይዛችሁት እንደሆነ፥ ተሳስታች
ኋል። መንገዱ ግን የያዛችሁት አይደለም።
7 እኛ ከሰበክንላችሁ ወንጌል በስተቀር፥ወደ
መንግሥተ ሰማይ የሚያደርሳችሁ ሌላ መን
ገድ ስለሌለ፥ እውነቱን በሐሰት በሚለው
ጡና የክርስቶስን ወንጌል በሚያጣምሙ
ሰዎች አሳብ እንዳትታለሉ ተጠንቀቁ።
8 ማንም ሰው፥እኔም ሆንኩ ወይም ከሰ
ማይ የወረደ መልአክ ቢሆን፥ቀድሞ ካስተ
ማርናችሁ ወንጌል የተለየ ሌላ ትምህርት
የሚያስተምራችሁ ከሆነ፥የተረገመ ይሁን።
9 ይህን እደግመዋለሁ፤ማንም ቀድሞ ከተቀ
በላችሁት የወንጌል ቃል የተለየ ሌላ ትምህ
ርት ቢሰብክላችሁ፥የተረገመ ይሁን።
10 ይህንንም ስላችሁ፥ እናንተን ለማስደ
ሰት ስል፥ ቃላት አጣፍጬ ልሸነግላችሁ
እንዳልፈለግሁ፥በግልጽ የሚታይ ነው። ሰዎ
ችን መሸንገልና ማስደሰት ብፈልግ ኖሮ፥
የክርስቶስ አገልጋይ ባልሆንኩ ነበር።
11 ወንድሞቼ ሆይ፥የሰበክሁላችሁ የወን
ጌል ቃል፥ ሰው ሠራሽ ሕግ እንዳይመስላ
ችሁ። 12 የገለጠልኝ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ
እንጂ፥ከሰው የተቀበልኩት ወይም የተማር
ኩት፥አይደለም።
13 ቀድሞ የአይሁድ እምነት ተከታይ
በነበርኩበት ጊዜ፥ክርስቲያኖችን ለማጥፋት
ከዋሉበት አሳሳድር፥ካደሩበት አላውል እያ
ልኩ፥ እንዴት አሳድዳቸው እንደ ነበረ
ታውቃላችሁ። 14 ለሃይማኖቱ ቀናተኛ የሆነ
በአገር ይፈለግ ቢባል፥ ከዕድሜ አቻዎቼ
መካከል የሚስተካከለኝ አልነበረም። ሲወ
ርድ ሲዋረድ የመጣውን የአይሁድ ሃይማኖ
ታዊ ሥርዓት ለመጠበቅ ቢሆንስ፥ማን ደርሶ
ብኝ!
15 ነገር ግን፥ገና በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ፥
ምሕረቱና ቸርነቱ የማያልቅ አምላክ፥አገል
ጋዩ እንድሆን በጸጋው መረጠኝ። 16 የል
ጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ከገለጠ
ልኝ በኋላ ለአሕዛብ ሁሉ የምሥራቹን እን
ዳበሥር አበቃኝ። ለዚህ ታላቅ ሥራ በተመ

ራሁም ጊዜ ከማንም ሰው ጋር አልተማከር
ኩም። 17 ሌላው ቀርቶ፣ከእኔ በፊት ሐዋር
ያት ከነበሩት ጋር እንኳ ለመማከር፣ ወደ
ኢየሩሳሌም አልሄድኩም ፤ የሄድኩት በቀ
ጥታ አረብ አገር ወደሚገኘ ወደ አንድ
በረሃ ነው። ከዚያም ተመልሼ ወደ ደማስቆ
አመራሁ። 18 ከሦስት ዓመት በኋላ፣ ጴጥሮ
ስን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ሄጄ ከእርሱ
ጋር ሁለት ሳምንት ያህል ሰነበትኩ።
19 እዚያ በሰነበትኩባቸው ቀናት ውስጥ፣
ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በስተቀር ከሌሎች
ሐዋርያት ጋር አልተገናኘሁም። 20 ይህ
የምነግራችሁ ሁሉ ሐሰት እንዳልሆነ ምስ
ክሬ እግዚአብሔር ራሱ ነው። 21 ከዚህ
በኋላ ወደ ሶሪያና ወደ ኪልቅያ ምድር
ሄድኩ። 22 በይሁዳ ከሚኖሩት ክርስቲያኖች
ጋር ዓይን ለዓይን ስላልተያየን፣ስሜን እንጂ
መልኬን አያውቁትም ነበር።
23 ስለ እኔ የሚያውቁት ነገር ቢኖር፣
«ያ ቀድሞ ሲያሳድደን የነበረው ሰው፣ካላ
ጠፋሁት ብሎ በጠላትነት የተነሣበትን
እምነት፣ አሁን ሽንጡን ገትሮ ይሰብካል»
እያሉ ሰዎች የነገሩቸውን ብቻ ነበር።
24 በእኔም ምክንያት፣ ለእግዚአብሔር ከፍ
ያለ ምስጋናና ክብር ያቀርቡ ነበር።

## ምዕራፍ 2

1 ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ፣ከበርናባስ
ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሼ ሄድኩ።
ቲቶም አብሮን ነበር። 2 ወደዚያም የሄድኩ
በት ምክንያት፣ በአሕዛብ መካከል ስለሰበክ
ሁት ወንጌል በዚያ ለሚገኙ ወንድሞች እን
ድገልጽላቸው፣ ጌታ ስላዘዘኝ ነበር። እዚ
ያም፣ዋና ዋናዎቹን የቤተ ክርስቲያን መሪ
ዎች ሁሉ ሰብስቤ ስለአገልግሎቴ ለብቻ
ነገርኳቸው። ይህንንም ያደረግሁት፣ እስካ
ሁን የፈጸምኩትንና ወደፊትም የምፈጽመ
ውን አገልግሎት ትክክለኛነት በማረጋገጥ
ከስሕተት ለመጠበቅ ነው። 3 እነርሱም ነገ
ሩን በደስታ ከመቀበላቸው የተነሣ፣አብሮኝ
የመጣው ከግሪክ ወገን የነበረው ቲቶ
እንኳ፣መገረዝ አለበት ብለው ሊያስገድዱት
አልፈለጉም።
4 ቀድሞውንም ቢሆን፣ ‘ከእኛ ወዲያ
ክርስቲያን ለአሳር ነው’ ብለው የሚመጻ
ደቁ አንዳንድ ሐሰተኞች፣የአይሁድን ሕግና
ሥርዓት እንዳለ የምንጠብቅ መሆን አለመ
ሆናችንን ለመሰለልና በክርስቶስ ኢየሱስ
ያገኘነውን ነፃነት ለመንፈግ በመካከላችን
ሾልከው ባይገቡ ኖሮ፣አገር አቋርጦ መጥቶ
ማስረዳቱ ባላስፈለገንም ነበር። 5 ሆኖም፣
እኛ ለዚህ ትምህርታቸው አፍታ ያህል
እንኳ አልተረታንላቸውም። ይህንንም ያደረ
ግነው፣ ደኅንነት የሚገኘው የግዝረትን ሥር
ዓት በመፈጸምና የኦሪትን ሕግ በመጠበቅ
መስሏችሁ፣እናንተ ግራ እንዳትጋቡና ከወን
ጌል እውነት ፈቀቅ እንዳትሉ ምሳሌ ልንሆ
ንላችሁ ነው።
6 እነዚያም የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ
መሪዎች፣ እኔ ባስተማርኩት የወንጌል ቃል
ላይ፣ ‘ጐድሎበታል’ ብለው የጨመሩት
አንዳችም ነገር አልነበረም። ደግሞም እኮ፣
እነርሱ፣ «ታላቅ» ተብለው ስለ መጠራታ
ቸው የምሰጠው የተለየ ግምት የለኝም።
እግዚአብሔር መልክ አይቶ አይፈርድምና።
7-9 እንዲያውም የቤተ ክርስቲያን ምሰሶ
ዎች በመባል የታወቁት ያዕቆብ፣ጴጥሮስና
ዮሐንስ፣ እግዚአብሔር አሕዛብን ለማዳን
እኔን መሣሪያው አድርጎ የቱን ያህል እንደ
ተገለገለብኝ ለመገንዘብ በቅተዋል። ጴጥሮስ
ለአይሁድ የወንጌልን ቃል እንዲሰብክ ሐዋ
ርያ ሆኖ እንደተመረጠ፣እግዚአብሔር እኔ
ንም የወንጌሉን ቃል የአሕዛብ ወገን ለሆ
ኑት እንድሰብክ፣ሐዋርያ አድርጎ የመረጠኝ
መሆኑን ለማወቅ ችለዋል። ለአይሁድ ወንጌ
ልን እንዲሰብክ ጴጥሮስን በሐዋርያነት የተ
ጠቀመው እግዚአብሔር፣ ለአሕዛብ ወንጌ
ልን እንድሰብክ እኔንም ደግሞ በሐዋርያ
ነት ተጠቅሟልና። ስለዚህም እነርሱ ለአይ
ሁድ፣እኛም ለአሕዛብ እንድናስተምር ከተ
ስማማን በኋላ እኔንና በርናባስን አበረታተ
ውን፣ እጅ ለእጅ ተጨባብጠን ተለያይተ
ናል። 10 የጠሉብን አደራ ቢኖር፣ ችግረኞ
ችን እንድናስባቸውና እንድንረዳቸው ብቻ
ነበር። ይህ ደግሞ እኔም ከልብ ያሰብኩበት
ጉዳይ ነበር።
11 ጴጥሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ
ግን ስለሠራው ስህተት ፊት ለፊት ወቅሼዋ
ለሁ። 12-13 ምክንያቱም፣ መጀመሪያ እዚያ
እንደመጣ ግዝረትንና ሌላውንም የአይሁድ
ሥርዓት ከማይከተሉ፣ ነገር ግን የክርስትናን
እምነት ከተቀበሉ የአሕዛብ ወገን ከሆኑ
ሰዎች ጋር አብሮ ሲበላ ከርሞ፣ኋላ ደግሞ፣
‘ግዝረት ለደኅንነት የግድ አስፈላጊ ነው’
የሚሉ፣የክርስትናን እምነት የተቀበሉ አይ
ሁድ ከኢየሩሳሌም ከያዕቆብ ዘንድ ሲመጡ
እነርሱን በመፍራት፣ ከአሕዛብ ወገን ከሆኑ
አማኞች ጋር መብላቱን ተወው። አብረ
ውት የነበሩ ወደ ክርስትና እምነት የተመ
ለሱ አይሁዶችም፣በርናባስንም ጨምሮ፣የጴ

ጥሮስን ግብዝነት ተከትለው፥ከአሕዛብ ጋር
አንድ ላይ ማዕድ መቁረሱን ተዉት።
[14]እኔም ይህንን ሁኔታ ካየሁና፥በሚያም
ኑት ነገር የማይጸኑ መሆናቸውን ካረጋገ
ጥሁ በኋላ፥በሁሉም ፊት ጴጥሮስን እንዲህ
አልኩት፤ «ምንም እንኳ ትውልድህ አይሁ
ዳዊ ቢሆንም፥የአይሁድን ሥርዓት ከተውክ
ቆይቷል። ታዲያ እንዲህ በአንድ ጊዜ ተለ
ውጠህ 'አሕዛብ የአይሁድን ሥርዓት ይጠ
ብቁ' ለማለት ያደረሰህ ምንድን ነው?
[15]አንተም እኔም ከአይሁድ ወገን መወለዳ
ችን የማይካድ ነገር ነው። 'ኃጢአተኞች'
ከሚባሉ ከአሕዛብ ወገን አይደለንም።
[16]ይሁን እንጂ፥እኛ የክርስትናን እምነት
የተቀበልን አይሁድ፥መጽደቅ የሚቻለው
ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን እንጂ፥የኦሪትን
ሕግ በመጠበቅ እንዳልሆነ አሳምረን እናው
ቃለን። እኛም፥እግዚአብሔር በእምነት
እንጂ የኦሪትን ሕግ በመጠበቅ እንደማያጽድ
ነን በመገንዘብ፥እምነታችንን በክርስቶስ ላይ
ጥለናል። ማንም ሕግን በመጠበቅ ሊድን
አይችልምና።»
[17]«እኛ አይሁዶች በክርስቶስ ለመጽ
ደቅ ስንፈልግ፥እኛም እንደ አሕዛብ ኃጢአ
ተኞች መሆናችንን የምንገነዘብ ከሆነ፥ከክር
ስቶስ ያተረፍነው ኃጢአተኝነታችንን መረ
ዳት ብቻ ነውን?» ይህን የምንል ከሆነ
ነገሩ ትክክል ስላይደለ፥እንዲህ ያለውን
ነገር ከማሰብ እግዚአብሔር ይጠብቀን።
[18]ያን የተውነውን የኦሪት ሥርዓት መልሰን
ለማቆም ብንሞክር ሕግ አፍራሾች ሆነን እን
ገኛለን። [19]እኔ በሕግ አማካይነት ለኦሪት
ሕግ የሞትኩ ነኝ። በሕይወት የምኖረው
በእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔርም ነው።
[20]ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬ ሞቻለሁ።
ይህ በመሆኑ፥ከእንግዲህ ወዲህ በእኔ ውስጥ
የሚኖረው፥ክርስቶስ ነው እንጂ እኔ ራሴ
አይደለሁም፤ አሁንም በሥጋዬ የምኖረው
ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔም በሞተው በእግ
ዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው።
[21]ጽድቅ የሚገኝበትን የክርስቶስን ሞት፥
አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት፥በማቃ
ለል የምመለከተው አይደለሁም። የኦሪትን
ሕግ በመፈጸም መዳን የምንችል ቢሆን
ኖሮ፥ክርስቶስ መሞት ባላስፈለገውም
ነበር።

## ምዕራፍ 3

[1]እናንተ የማታስተውሉ የገላትያ
ሰዎች! እንዲህ አድርጎ ያሳታችሁ ማነው?
ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዴት እንደ
ሞተ፥እንደ ሥዕል ቁልጭ ብሎ እንዲታያ
ችሁ አላደረግሁም ነበር? [2]እስቲ አንድ
ነገር ልጠይቃችሁ። ለመሆኑ መንፈስ ቅዱ
ስን የተቀበላችሁት የኦሪትን ሕግ ለመፈ
ጸም ባደረጋችሁት ጥረት ነው? ወይስ የተሰ
በከላችሁን የወንጌል ቃል በእምነት በመቀ
በላችሁ ነው? [3]በመጀመሪያውኑ የኦሪትን
ሕግ በመጠበቅ መንፈሳዊ ሕይወት ልታገኙ
አለመቻላችሁን አውቃችሁ በእምነት ከጀ
መራችሁ በኋላ፥ተመልሳችሁ ይህንኑ ሕግ
በመጠበቅ 'መንፈሳዊ ሕይወታችን ፍጹም
ይሆናል' ብላችሁ እንዴት ታስባላችሁ?
ሞኞች ናችሁ ልበል? [4]በወንጌል ምክን
ያት ብዙ መከራ እንደ ተቀበላችሁ አውቃ
ለሁ። ታዲያ ይህ ሁሉ ከንቱ ሆኖ ይቅር?
ማመኑ ቸገረኝ።
[5]እስቲ አሁንም ደግሜ ልጠይቃችሁ?
ለመሆኑ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን
ኃይል የሰጣችሁና በመካከላችሁ ተአምራ
ትን የሚያደርግላችሁ፥የኦሪትን ሕግ በመጠ
በቃችሁ ነው? ይህን እናንተም አትሉት።
ይህ ሁሉ የተደረገላችሁ፥ክርስቶስን በፍ
ጹም ልባችሁ ስላመናችሁ ብቻ ነው።
[6]እስቲ አብርሃምን እንደ ምሳሌ ውሰ
ዱት። እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ በማ
መኑ ብቻ፥እንደ ጻደቀ በመጽሐፍ ተነግሮለ
ታል። [7]የአብርሃም ልጆች የምንላቸው፥በእ
ምነት የሚመላለሱትን መሆኑን አትርሱ።
[8-9]ቅዱሳት መጻሕፍት፥እግዚአብሔር
አሕዛብን በእምነት እንደሚያጸድቃቸው
አስቀድመው ተናግረዋል። እግዚአብሔር
ከዘመናት በፊት «የዓለም ሕዝብ ሁሉ በአ
ንተ ይባረካሉ» ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም
በቅድሚያ ሰብኮለታል። በዚህም መሠረት፥
ዛሬ በክርስቶስ የሚያምኑና የሚታመኑበት
ሁሉ፥አብርሃም የተቀበለውን በረከት እነር
ሱም ይቀበላሉ።
[10]'የኦሪትን ሕግ በመፈጸም እንጸድቃ
ለን' የሚሉ ሁሉ ከእርግማን በታች
ናቸው። ምክንያቱም በራሱ በኦሪት፥«በማ
ናቸውም ጊዜ ከትእዛዛቱ አንዲቱን እንኳ
የሚያፈርስ ማንም ሰው፥የተረገመ ይሁን»
ተብሎ በግልጽ ተጽፏል። [11]የኦሪት ሕግ
ማንንም በእግዚአብሔር ፊት አያጸድቅም።
ምክንያቱም፥«ጻድቅ በእምነት ይኖራል»
ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏልና።
[12]'ከትእዛዛቱ አንዲቱን እንኳ ሳይሽር የሚ
ጠብቅ ይድናል' ከሚለው ከኦሪቱ ሕግ፥ይህ
በእምነት የመዳኑ ጉዳይ የቱን ያህል የተለየ

መሆኑን ፣ እስቲ ራሳችሁ ተመልከቱት።
13 «በእንጨት ላይ የተሰቀለ የተረገመ
ነው» ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ
ተጻፈ ፣ ክርስቶስ ስለኛ እርግማን ሆኖ ፣ የኦሪ
ትን ሕግ ካለመጠበቅ ከሚደርስብን እርግ
ማን ዋጅቶ ፣ ነፃ አድርጎናል።
14 የዋጀንም ፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም
የሰጠውን በረከት ፣ አሕዛብም በክርስቶስ ኢየ
ሱስ እንዲወርሱ ነው። እኛም በተሰጠን
ተስፋ መሠረት ፣ በእምነት መንፈስ ቅዱስን
እንቀበላለን። 15 ወንድሞቼ ሆይ ፣ በሰዎች
መካከል እንኳ ሲደረግ እንደምታዩት ፣
አንድ ሰው ወዶ የተዋዋለውንና በፊርማው
ያጸደቀውን ውል ፣ ሊያፈርሰው አይችልም።
እንዲሁም እግዚአብሔር ፣ «አደርግላችኋ
ለሁ» ብሎ የሰጠውን ተስፋ ፣ ከመፈጸም
ወደ ኋላ የሚል አይደለም።
16 እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለልጁ
ተስፋ ሰጥቷቸዋል። «ተስፋ ሰጠ» ሲል ፣
«ለአብርሃምና ለልጁ ሰጠ» ይላል እንጂ ፣
«ለአብርሃምና ለልጆቹ ሰጠ» አላለም።
«ለአብርሃምና ለልጆቹ ሰጠ» ቢል ኖሮ ፣
ቃሉ ከአይሁድ ወገን የሆኑትን በሙሉ ባጠ
ቃለለ ነበር። ነገር ግን ፣ በነጠላ ፣ «ለልጁ»
ስለሚል ፣ የተነገረው ቃል ለክርስቶስ ብቻ
እንደሆነ ማስተዋል ይገባል። 17 እግዚአብ
ሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል ፣ ከአራት መቶ
ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠ የኦሪት ሕግ
ሊሽረው ወይም ሊለውጠው አይችልም።
18 እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል የገባው
እርስት ፣ በሕግ ላይ የተመሠረተ ቢሆን ኖሮ
'የተስፋ ቃል' የሚለው ነገር ቦታ ባልኖረ
ውም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እርስ
ቱን ለአብርሃም የሰጠው በተስፋ ቃል መሠ
ረት ነው።
19 ይህ ከሆነ ሕግ ለምን ተሰጠ? የኦሪት
ሕግ ከተስፋው በኋላ የተሰጠበት ምክን
ያት ፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ አፍራ
ሾች መሆናቸውን ይረዱ ዘንድ በተጨማሪ
እንዲያገለግል ነው። እግዚአብሔር ለአብር
ሃም ተስፋ የሰጠው ዘር ክርስቶስ በመጣ
ጊዜ ፣ የኦሪት ሕግ አብቅቷል። እግዚአብ
ሔር ሕጉን የሰጠው በመላእክት በኩል ፣
ማዕከላዊ በሆነ በአንድ ሰው አማካይነት
ነበር። 20 ማዕከላዊ የሆነ ሰው የሚያስፈል
ገው በሁለት ወገኖች መካከል ነው። ነገር
ግን ተስፋውን የሰጠው እግዚአብሔር
አንድ ነውና የገባውን ተስፋ ለመፈጸም ፣
ማዕከላዊ ሰው አላስፈለገውም።
21-22 ታዲያ ፣ የእግዚአብሔር ሕግና የእግ
ዚአብሔር ተስፋ ፣ እርስ በርሳቸው ይቃረ
ናሉ ማለት ነው? በፍጹም አይቃረኑም!
ሕይወትን መስጠት የሚችል ሕግ ተሰጥቶን
ቢሆን ኖሮ ፣ ጽድቅ በሕግ በተገኘ ነበር።
ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በእም
ነት የሚገኘው ጽድቅ ለሚያምኑ ብቻ
ይሰጥ ዘንድ ፣ መጽሐፍ ሰዎች ሁሉ የኃጢ
አት ባሪያዎች መሆናቸውን ይናገራል።
23 ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም እስከ መጣበ
ትና ፣ እምነት እስከ ተገለጠበት ጊዜ ድረስ ፣
ሕግ የኃጢአት እሥረኛ አድርጎ ይዞን
ነበር።
24 ክርስቶስ መጥቶ ፣ በእምነት ጽድቅን
እስካገኘንበት ጊዜ ድረስ ፣ ሕግ መሪያችንና
ሞግዚታችን ነበር። 25 አሁን ግን ክርስቶስ
ስለ መጣ ፣ በሕግ ሞግዚትነት ሥር መተዳ
ደር የሚያስፈልገን ሆኖ አልተገኘም።
26 ክርስቶስን በማመናችን ሁላችንም የእግዚ
አብሔር ልጆች ሆነናል። 27-28 ምክንያ
ቱም ፣ ከክርስቶስ ጋር አንድነት እንዲኖረን
የተጠመቅን ሁሉ ፤ ክርስቶስን ለብሰነዋልና።
ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ፣ 'ይህ አይሁዳዊ
ነው ፤ ይህ አሕዛብ ነው' ወይም ፤ 'እገሌ
ባሪያ ነው ፤ እገሌ የጨዋ ልጅ ነው' ወይም
ደግሞ ፤ 'እገሊት ሴት ናት ፤ እገሌ ወንድ
ነው' የሚል ልዩነት በመካከላችን የለም።
ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ሆነናል። 29 እን
ግዲህ የክርስቶስ ከሆንን ደግሞ ፣ እውነተ
ኞች የአብርሃም ልጆች ነን። በተስፋ ቃል
መሠረትም ወራሾች ነን ማለት ነው።

## ምዕራፍ 4

1 እስቲ አንድ ሰው ፣ ያለ የሌለ ሀብቱንና
ንብረቱን ለልጁ ትቶለት ሞተ እንበል።
ወራሽ ልጁ ሕፃን ከሆነ ፣ ምንም እንኳ የው
ርስ መብቱ የተጠበቀ ቢሆንም ፣ ለአቅመ
አዳም እስካልደረሰ ድረስ ፣ በሀብት በንብረቱ
ለማዘዝ ፣ ሥልጣን የለውም። 2 ንብረቱን እን
ዲረከብ አባቱ በኑዛዜው ላይ የወሰነለት ጊዜ
እስኪደርስ ፣ የሞግዚቶቹንና የመጋቢዎቹን
ፈቃድ እየፈጸመ ያድጋል።
3 ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ
በፊት ፣ የእኛም ሁኔታ እንደዚሁ ነበር። ለማ
ያድነው የዚህ ዓለም ሥርዓት ፣ ባሮች ሆነን
ስንገዛ ኖረናል። 4 ነገር ግን እግዚአብሔር
የወሰነው ጊዜ ሲደርስ ፣ ልጁን ልኮ የአይ
ሁድ ወገን ከምትሆን ሴት እንዲወለድ አደ
ረገ። 5 እርሱም ፣ በሕግ ዘመን ተወልዶ
ከሕግ የባርነት ቀንበር ነፃ በማውጣት ፣ የእግ

ዚአብሔር ልጆች አደረገን። 6 እግዚአብሔ
ርም፥ ልጆቹ በመሆናችን፥እርሱን «አባባ»
ብለን ለመጥራት የምንችልበትን፥ የልጁን
የኢየሱስ ክርስቶስን መንፈስ፥ በልባችን
ውስጥ አኑሮልናል። 7 ከእንግዲህ ወዲህ፥የእ
ግዚአብሔር ልጆች ነን እንጂ፥ ባሪያዎች
አይደለንም። እግዚአብሔር ልጆቹ እንድን
ሆን ስለፈቀደልንም፥የእርሱ የሆነው ሁሉ
የእኛ ነው።

8 እግዚአብሔርን ከማወቃችሁ አስቀ
ድሞ፥የማዳን ኃይል ለሌላቸው አማልክት፥
በባርነት ስትገዙ ኖራችኋል። 9 አሁን ግን
እውነተኛውን አምላክ አውቃችሁታል።
እርሱም አውቆአችኋል። ታዲያ አሁን፥እን
ዴት ደካማ ለሆነና ወደ እግዚአብሔር ሊያ
ደርሳችሁ ለማይችል የዚህ ዓለም ሥርዓት፥
ተመልሳችሁ ትገዛላችሁ? እንዴትስ፥ ወደ
ኋላ ተመልሳችሁ፥ከኦሪት ሕግ በታች ባሪያ
ሆኖ ለመኖር ትፈልጋላችሁ? 10 ቀናትንና
ወራትን ቆጥራችሁ፥ወቅቶችንና ዓመታትን
ለይታችሁ በማክበርስ፥እንዴት እግዚአብሔ
ርን ደስ ለማሰኘት ትሞክራላችሁ? 11 እንግ
ዲህ ነገሩ ሁሉ እንደዚህ ከሆነ፥የሚያሳስብ
ነው። ድካሜም፥ልፋቴም ሁሉ፥ፍሬ አልሰ
ጠም ማለት ነው።

12 እኔ አይሁዳዊ ሳለሁ እናንተን ከመሰ
ልኩ፥ እናንተም ከሕግ ባርነት ነፃ በመው
ጣት እኔን ምሰሉ። ከእናንተ ጋር በነበርኩ
በት ጊዜ ምንም አልበደላችሁኝም። 13 እን
ደምታውቁት በመጀመሪያ ወንጌልን ልሰብ
ክላችሁ የመጣሁት በሕመም ምክንያት
ነበር። 14 ሆኖም ሕመሜ ለእናንተ ፈተና
ቢሆንባችሁም እንኳን፥ በሽተኛ ነው ብላ
ችሁ አልናቃችሁኝም። እንደ እግዚአብ
ሔር መልአክ፥አልፎ ተርፎም እንደ ራሱ
እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ፥አክብራችሁ ተቀብ
ላችሁ ተንከባክባችሁኛል።

15 ያ ሁሉ አብረን ያሳለፍነው የደስታ
ጊዜስ፥ እንዴት ተረሳ? ያን ጊዜ ሌላው
ቀርቶ፥ «ዓይናችሁን እንኳ አውጥታችሁ
ስጡኝ» ብላችሁ ኖሮ፥ ይህንኑ ከማድረግ
ወደ ኋላ እንደማትሉ በሚገባ አውቃለሁ።

16 ታዲያ እውነት በመናገሬ ጠላት
መስዬ ታየኋችሁ ልበል?

17 እነዚያ ወደ ስሕተት የሚገፉችሁ
አስተማሪዎች፥የሚጠቀሙአችሁና በጎ ነገር
የሚያስቡላችሁ እንዳይመስሏችሁ። ጥረታ
ቸው ሁሉ እናንተና እኔ ተቆራርጠን እንድ
ንቀር ለማድረግ ነው። እናንተና እኔ ተቆራ
ርጠን መቅረታችንን የሚፈልጉትም፥እነርሱ
የሚነግሩዋችሁን ብቻ 'አሜን' እያላችሁ
እንድትቀበሉዋቸው ለማድረግ እንዲረዳ
ቸው ነው። 18 ጥሩ ነገር ለማድረግ ፍላጐት
ማሳየቱ፥ በጣም መልካም ነው። ይሁን
እንጂ ይህ ፍላጐት፥እኔ አብሬአችሁ ሳለሁ
ብቻ ሳይሆን፥ ሁልጊዜም ሊኖራችሁ ይገ
ባል። 19 ልጆቼ ሆይ፥ ልባችሁን እንደ
ዙፋን ዘርግታችሁ፥እንደገና ለክርስቶስ እስ
ክትሰጡት ድረስ፥ልክ ምጥ እንደያዛት ሴት
ተጨንቄአለሁ። 20 በዚች በአሁኗ ሰዓት፥ከእ
ናንተ ዘንድ ሆኜ ድምፄን አለስልሼ ብነግራ
ችሁ፥ የቱን ያህል ደስ ባለኝ ነበር። ነገር
ግን፥ የቦታ ርቀት ስለወሰነን የማደርገው
ግራ ገብቶኛል።

21 የኦሪትን ሕግ በመጠበቅ፥ 'ደኅንነትን
እናገኛለን' የምትሉ ወዳጆች ሆይ! እስቲ
ንገሩኝ? ለመሆኑ ሕጉ ምን እንደሚል በእ
ርግጥ አውቃችኋል? 22 አብርሃም፥ አንዱ
ከነፃይቱ ሴት፥ሁለተኛው ከአገልጋይቱ ሴት
የተወለዱ፥ ሁለት ወንዶች ልጆች እንደነበ
ሩት በመጽሐፍ ተጽፏል። 23 ከአገልጋይቱ
የተወለደው ልጅ፥እንደ ማናቸውም ሕፃን፥
የተፈጥሮን ሥርዓት ጠብቆ የተወለደ
ሲሆን፥ ከነፃይቱ ሴት የተወለደው ግን፥እግ
ዚአብሔር አስቀድሞ በሰጠው የተስፋ ቃል
መሠረት ነው።

24-25 ይህም ታሪክ ሁለት ነገሮችን ያስተ
ምረናል። ሁለቱ ሴቶች፥የሁለቱ ቃል ኪዳን
ምሳሌዎች ናቸው። አንዱ ቃል ኪዳን፥
በሲና ተራራ ላይ በሙሴ አማካይነት የተሰ
ጠው ነው። አጋር የዚህ ቃል ኪዳን ምሳሌ
ነች። እንደዚሁም አጋር በአረብ አገር የሚ
ገኘው የሲና ተራራና የአሁኗ ምድራዊት
ኢየሩሳሌም ምሳሌ ናት። ይህች ከተማ 'የኦ
ሪትን ሕግ በመጠበቅ እግዚአብሔርን ደስ
አሰኝቶ መጽደቅ ይቻላል' ለሚለው ሥር
ዓት እምብርት ናትና። ያንንም ሥርዓት
በሥራ ላይ ለማዋል የሚጣጣሩ ሁሉ፥የባር
ነት ቀንበር ያልወረደላቸው ልጆቿ
ናቸው። 26 የእኛይቱ ከተማ ኢየሩሳሌም
ግን፥ ለአይሁድ ሕግ በባርነት የማትገዛ ነፃ
ይቱ ሰማያዊት ከተማ ናት። እኛም የእርሷ
ልጆች ነን።

27 ነቢዩ ኢሳይያስ፥ «አንቺ መካን ደስ
ይበልሽ፤ አንቺ ከዚህ ቀደም ምጥ ያላየሽ
እልል በዪ። ብቸኛ የሆነችው ሴት ልጆች፥
ባል ካላት ሴት ልጆች ይበልጣሉና» ያለው
በዚህ ምክንያት ነበር።

28 ውድ ወንድሞቼ ሆይ፥እኔና እናንተ
እንደ ይስሐቅ የተስፋው ልጆች ነን። 29 ስለ

ዚህ በዚያን ጊዜ በተፈጥሮ ሥርዓት የተወለ
ደው እስማኤል፣በመንፈስ ኃይል የተወለደ
ውን ይስሐቅን እንዳሳደደው ሁሉ፣ዛሬም
«የኦሪት ሕግ የበላይ ጠባቂዎች ነን»
የሚሉ አይሁድ፣እኛን ያሳድዱናል።
30 ነገር ግን እግዚአብሔር አብርሃምን፣
«ከአገልጋይቱ ሴት የወለድከው ልጅ፣ከነፃ
ይቱ ሴት ከወለድከው ልጅ ጋር ርስትን
መካፈል ስለማይገባው፣አገልጋይቱን ከነል
ጅዋ አስወጥተህ ስደዳት» ሲል እንደነገረው
በመጽሐፍ ተጽፏል። 31 የተወደዳችሁ ወን
ድሞቼ ሆይ፣እኛ በነፃይቱ ሴት በሣራ የተ
መሰለው የወንጌል ልጆች ነን እንጂ፣በአገል
ጋይቱ ሴት በአጋር የተመሰለው የኦሪት
ሕግ ተገዢዎች አይደለንም።

## ምዕራፍ 5

1 ክርስቶስ አርነት ያወጣን በነፃነት ለመ
ኖር ስለሆነ፣ከእንግዲህ ወዲህ ጸንታችሁ
ቁሙ እንጂ፣ዳግመኛ ለኦሪት ሕግና ሥርዓ
ቶቿ፣ባሪያ ሆናችሁ አትገዙ። 2 እኔ ጳው
ሎስ የምነግራችሁን ልብ በሉ። የኦሪትን
ሕግ በመጠበቅና፣የግዝረትን ሥርዓት በመ
ፈጸም፣ለመጽደቅ የምትፈልጉ ከሆነ፣ክርስ
ቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። 3 «መገረዝ
ያጸድቃል» ብሎ የሚያምን ሁሉ፣የኦሪት
ንም ሕግና ሥርዓት በሙሉ የመፈጸም
ግዴታ አለበት። 4 እናንተ ሕግ በመጠበቅ
ለመጽደቅ የምትሞክሩ ሁሉ ከክርስቶስ የራ
ቃችሁና የእግዚአብሔርም ጸጋ የተለያችሁ
ናችሁ።
5 ነገር ግን እኛ፣ተስፋ የምናደርገውን
ጽድቅ፣በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት በእምነት
እንጠብቀዋለን። 6 ከክርስቶስ ጋር ሕብረት
ካለን፣በመገረዝ የሚገኝ ጥቅም፣ባለመገረ
ዝም የሚመጣ ጉዳት፣የለም። ቁም ነገሩ፣
ፍቅርን በሥራ የሚገልጽ እምነት መቀዳጀ
ታችን ነው። 7 ከዚህ በፊት የነበረው መንፈ
ሳዊ ሕይወታችሁ ደህና መንገድ የያዘ
ነበር። ታዲያ አሁን እውነትን እንዳትከተሉ
ያደረጋችሁ ማነው? 8 'እንዲህ ያደረገን እግ
ዚአብሔር ነው' እንዳትሉ፣በክርስቶስ ወደ
ተገኘው ነፃነት የጠራችሁ እርሱ ራሱ ስለ
ሆነ፣እርሱ ይህን አያደርገውም። 9 እንደም
ታውቁት ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካ
ዋል። እንደዚሁም፣እናንተንም እንዲህ
ባለው ክፉ ትምህርት ለመመረዝ፣አንድ
የተሳሳተ ሰው በመካከላችሁ ከገባ፣ይበ
ቃል።
10 እኔ የማምነውን እናንተም እንድታ
ምኑ፣እግዚአብሔር ልቦናችሁን እንደሚያበ
ራው አልጠራጠርም። ማንም ይሁን ማን፣
እንዲህ አድርጎ ያሳሳታችሁ ሰው፣እንዲሁ
የሚቀር አይደለም፤ፍርዱን ከእግዚአብሔር
ይቀበላል።
11 አንዳንድ ሰዎችማ እኔ፣«ለመዳን የግ
ዝረትን ሕግ መፈጸምና የኦሪትን ሕግ መጠ
በቅ ግድ አስፈላጊ ነው» ብዬ እንደሰበክሁ
አስመስለው እስከ መወሻከት ደርሰዋል።
እንዲህ ያለው ትምህርት ሰዎችን ስለማያስ
ቀይም፣ይህን ያህል ባልተጠላሁና ባልተሰደ
ድኩ፣የክርስቶስም መስቀል መሰናከያ ባል
ሆነባቸው ነበር። ነገር ግን፣እስከ አሁን
ድረስ በሰዎች እስከ መጠላትና እስከ መሰ
ደድ የደረስኩት፣«ደኅንነት የሚገኘው
በመስቀል ላይ በሞተው በክርስቶስ በማመን
ብቻ ነው» እያልኩ ስለሰበክሁ ብቻ ነው።
12 እነዚህ፣'ካልተገረዛችሁ አትድኑም'
እያሉ ከጸጋው ሊለይዋችሁ የሚፈልጉ
መምህራን፣ከእናንተ ወዲያ ርቀው ቢፈልጉ
ራሳቸው ይሰለቡ!
13 ወንድሞቼ ሆይ፣የተጠራችሁት በነፃ
ነት እንድትኖሩ ነው። ነገር ግን ያገኛችሁ
ትን ነፃነት፣የሥጋችሁን ፍላጐት ለማርካት
አትጠቀሙበት። በዚህ ፋንታ አንዱ ሌላ
ውን በፍቅር ያገልግለው። 14 ሕግጋቱ ሁሉ
በአንዲት ትእዛዝ ይጠቃለላሉ። ትእዛዚ
ቱም፣«ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ»
የምትል ናት። 15 ነገር ግን በመፋቀር
ፈንታ፣እርስ በርሳችሁ የምትበጫጨቁና
የምትነቃቀፉ ከሆነ፣አንዱ ሌላውን እንዳያ
ጠፋው ተጠንቀቁ።
16 አንድ ነገር ላሳስባችሁ። የመንፈስ
ቅዱስን አመራር ብቻ ተከተሉ። ይህን የም
ትከተሉ ከሆነ፣ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችሁን
ለማርካት ስትሉ የምኖት ባሪያ ሆናችሁ
አትገዙም። 17 ኃጢአተኛ ተፈጥሮ የሚመ
ኘው፣ለመንፈስ ቅዱስ አሳብ ተቃራኒ የሆነ
ውን ነው። መንፈስ ቅዱስም የሚያስበው
ከኃጢአተኛ ተፈጥሮ ጋር የማይመሳሰለውን
ነው። መንፈስና ሥጋ ምን ጊዜም እርስ
በርስ ጦርነት እንደገጠሙ ነው፣አይስማ
ሙም። ስለዚህ የምትፈልጉትን ለማድረግ
አትችሉም። 18 በመንፈስ ቅዱስ የምትመሩ
ከሆነ ግን፣ለኦሪት ሕግ ተገዢዎች አትሆ
ኑም።
19 የሥጋ ሥራዎች የታወቁ ናቸው። እነ
ርሱም፣ዝሙት፣ርኩሰት፣መዳራት 20 ጣዖ
ትን ማምለክ፣ምዋርተኝነት፣ጥላቻ፣አለመግ
ባባት፣ቅናት፣ቁጣ፣ራስ ወዳድነት፣መለያ

የት፥አድመኝነት፥ 21 ምቀኝነት፥መግደል፥
ስካር ፥ ዘፋኝነት–እነዚህንም የመሳሰሉት
ናቸው። ከዚህ በፊት እንደነገርኳችሁ
ሁሉ፥እነዚህን ኃጢአቶች የሚፈጽም፥የእግ
ዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ አይች
ልም።
22 የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ግን፥ፍቅር፥
ደስታ፥ሰላም፥ትዕግሥት፥ቸርነት፥በጎነት፥
ታማኝነት፥ 23 ትሕትና፥ ራስን መግዛት
ናቸው። እነዚህን የመንፈስ ፍሬዎች የሚ
ቃረን ሕግ የለም።
24 የክርስቶስ የሆኑት ሁሉ፥ሥጋን ከፍት
ወቱና ከክፉ ምኞቱ ጋር፥በመስቀል ላይ
ሰቅለው አስወግደውታል።
25 እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የም
ንኖር ከሆነ፥በእርሱ እንመራ። 26 ይህን ካደረ
ግን፥ከቅናትና ከመራራነት፥ከንቱ ክብርና
ከንቱ ውዳሴን ከመፈለግ እንገታለን።

## ምዕራፍ 6

1 የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ አንዱ
ክርስቲያን ወንድማችሁ በኃጢአት ወድቆ
ብታዩት፥እናንተ በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰ
ላችሁ፥በገርነትና በየዋህነት ወደ ትክክለኛ
ሕይወት እንዲመለስ፥ እርዱት። ይህ ዛሬ
በእርሱ ላይ የደረሰው ፈተና፥ከእናንተ በአ
ንዱ ላይ ሊደርስ የሚችል መሆኑን በመረ
ዳት ለራሳችሁም ተጠንቀቁ። 2 እርስ በእርሳ
ችሁ ተረዳዱ፤አንዱም የሌላውን ችግር ያቃ
ልለት። ይህን በማድረጋችሁም፥የክርስቶስን
ሕግ ትፈጽማላችሁ። 3 አንድ ሰው ማንነቱን
በሚገባ ሳይረዳ፥ራሱን ከፍ ከፍ ቢያደርግ፥
እንደዚህ ያለው ሰው ሌላውን ሳይሆን፥
ራሱን ያታልላል።
4 እያንዳንዱ ሰው ራሱን መርምሮ፥ማድ
ረግ የሚገባውን ትክክለኛ ነገር መፈጸሙን
ወይም አለመፈጸሙን ያረጋግጥ። ራሱንም
ከሌሎች ሳያወዳድር በራሱ ሥራ ብቻ
ሊረካ የሚችለውም፥ በዚያን ጊዜ ነው።
5 በዚህ ዓይነት እያንዳንዳችን የየራሳችንን
ሸክም መሸከም ይገባናል።
6 የእግዚአብሔርን ቃል የሚማሩ፥በሚች
ሉት ሁሉ አስተማሪዎቻቸውን መርዳት
ይገባቸዋል።
7 ማንም እንዳያታልላችሁ ተጠንቀቁ።
እግዚአብሔር መቀለጃም እንዳልሆነ፥
እወቁ። ሰው የሚያጭደው፥ያንኑ የዘራውን
ነው። 8 የሥጋ ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፥
ጥፋትን ያጭዳል። በመንፈስ የሚዘራ ግን፥
መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን የዘላለም ሕይ
ወት ይወርሳል። 9 ተስፋ ሳንቆርጥ በትዕግ
ሥት ብንጸና፥ ጊዜው ሲደርስ የበረከትን
መከር መሰብሰብ ስለምንችል፥በጎ ነገር ከማ
ድረግ አንቆጠብ። 10 በሚያጋጥመን ዕድል
ሁሉ በመጠቀም ለሰው ሁሉ፥በተለይም ለክ
ርስቲያን ወንድሞቻችን ደግ መሥራት ያለ
ብን ስለዚህ ነው።
11 እንዴት ባሉ ትላልቅ ፊደሎች በገዛ
እጄ እንደጻፍኩላችሁ ተመልከቱ። 12 «መገ
ረዝ አለባችሁ» ብለው የሚያስገድዷችሁ
መምህራን ይህን የሚሉበት ምክንያት፥
«ደኅንነት የሚገኘው በክርስቶስ መስቀል
ብቻ ነው» ብለው ቢያስተምሩ፥ መከራና
ስደት የሚመጣባቸው መሆኑን ስለሚያ
ውቁ፥ ከዚህ ለማምለጥና ሰውንም ለማስደ
ሰት ብለው ነው። 13 እናንተን «መገረዝ ይገ
ባችኋል» ብለው ያስተምሯችሁ እንጂ፥ራሳ
ቸው የኦሪትን ሕግ የሚፈጽሙ ሆነው አይ
ደለም። ዋና ፍላጐታቸው እናንተን፥ «ተከ
ታዮቻችን ናቸው» ብለው ለማውራትና በእ
ናንተ የሥጋ ግዝረት ለመመካት ነው።
14 እኔ ግን፥ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ
መስቀል በስተቀር፥የምመካበት ምንም ነገር
የለኝም። በዚያ መስቀል፥እኔ ለዓለም ሞቻ
ለሁ፤ ዓለምም ለእኔ ሞቷል። 15 እንግዲህ
መገረዝ የሚሰጠው ጥቅም፥ አለመገረዝም
የሚያመጣው ጉዳት፥እንደሌለ አውቀናል።
የሚጠቅመውስ በመንፈስ አዲስ ፍጥረቶች
ሆነን መገኘታችን ነው።
16 ይህችን ትእዛዝ ለምትከተሉና በዚሁ
መሠረት ለምትኖሩ፥የእግዚአብሔር ወገኖች
ለሆናችሁ ሁሉ፥ሰላምና ምሕረት እንዲበዛላ
ችሁ ምኞቴ ነው። 17 ከእንግዲህ ወዲህ
ማንኛችሁም በዚህ ጉዳይ ላይ፥ ከእኔ ጋር
ክርክር ለመግጠም እንዳትሞክሩ በጥብቅ
አሳስባችኋለሁ። ምክንያቱም በሥጋዬ የጌታ
ባሪያ መሆኔን የሚያመለክት ጠባሳ፥ከክርስ
ቶስ ጠላቶች በደረሰብኝ ግርፋት ተቀብያ
ለሁ።
18 ወንድሞቼ ሆይ፥ የጌታችን የኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።
አሜን!

የናንተው
ጳውሎስ

# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈው መልእክት

## መግቢያ

የመልእክቱ ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፥የተጻፈበትም ዘመን ከ62-64 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። ይህ መልእክት በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ የሚያገኙትን ሰማያዊ በረከት ያበሥራል። እግዚአብሔር ስለወደደን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ዋጅቶ ልጆቹ አደረገን፤አከበረንም። በሰማያዊ ርስቱም ዘላለማዊ ደስታን አዘጋጀልን። ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል ልዩ ልዩ ክፍሎች ስንሆን፥በመንፈስ ግን አንድ ነን። የአካሉ ልዩ ልዩ ክፍሎች ከመሆናችን የተነሣም፥ልዩ ልዩ በረከቶችንና ስጦታዎችን ለመቀበል ተጠርተናል።

---

## ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ፥የኢየሱስ ክርስ
ቶስ ሐዋርያ እንዲሆን ከተመረጠው ከጳው
ሎስ፥ በኤፌሶን ለሚገኙት በክርስቶስ ኢየ
ሱስ ለታመኑት ክርስቲያኖች የተላከ። 2 የእ
ግዚአብሔር አብ፥የጌታችንም የኢየሱስ ክር
ስቶስ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን።
3 በክርስቶስ ኢየሱስ፥ሰማያዊ የሆነውን መን
ፈሳዊ በረከትን ሁሉ እንድንሞላ ያደረገን፥
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአ
ብሔር የተመሰገነ ይሁን።
4 እኛን ያላንዳች ነውርና ያላንዳች
ነቀፋ፥ ቅዱሳን ሁነን በፊቱ እንድንኖር፥
ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በክርስቶስ መረ
ጠን። 5 እንደመልካም አሳቡና ፈቃዱም
በክርስቶስ ኢየሱስ ልጆቹ ሊያደርገን ወዶ
አስቀድሞ በፍቅር ጠራን። 6 እግዚአብሔር
ይህንን ያደረገው በውድ ልጁ በኩል በነፃ
ስለሰጠን አስደናቂ ጸጋ እኛ እናከብረውና
እናመሰግነው ዘንድ ነው። 7 ለምሕረቱና
ለቸርነቱ ወሰን የሌለው በመሆኑም፥ደኅንነ
ትን ባገኘንበት በልጁ ደም ከኃጢአት አን
ጽቶ፥ 8 በታላቅ ጥበቡና ዕውቀቱ የጸጋው
ብልጽግና እንዲያጥለቀልቀን አድርጓል።
9 በክርስቶስ ኢየሱስ ያቀደውንና ጊዜው
ሲደርስ ሊፈጸም ያለውን የፈቃዱን ምሥ
ጢር እናውቅ ዘንድ፥በበጎ አሳቡ ለእኛ ገል
ጾልናል። 10 ይህ የእግዚአብሔር እቅድ ምን
ድን ነው? እቅዱ፥ ጊዜው ሲደርስ በሰማ
ይም በምድርም ያለው ሁሉ፥ ከክርስቶስ
ሥልጣን ሥር እንዲውል እግዚአብሔር
መወሰኑ ነው። 11 ማናቸውንም ነገር በገዛ
ፈቃዱ የሚሠራው እግዚአብሔር፥ እርሱ
ራሱ ባቀደው መሠረት አስቀድሞ የወሰነ
ስለሆነ፥ ልጆቹ እንድንሆን በበጎ ፈቃዱ
ለመመረጥ በቅተናል። 12 ይህንንም ያደረገ
በት ምክንያት፥ ቀደም ብለን ክርስቶስን
ተስፋ ያደረግን እኛ፥ክብርና ምስጋና እንድ
ናቀርብለት ነው።
13 እናንተም፥ የእውነት ቃል የሆነውን
የደኅንነት ወንጌል ሰምታችሁ ክርስቶስን
ስላመናችሁ፥እግዚአብሔር ተስፋ በገባልን
በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋል። 14 እግዚአብ
ሔር፥የራሱ የሆኑትን የመጨረሻ ነፃነታቸ
ውን እስከሚያቀዳጃቸው ድረስ፥ ይህ መን
ፈስ ለምንወርሰው እርስት በልባችን የሚ
ኖር ዋስትና ነው። እግዚአብሔርም የርስቱ
ወራሾች የሚያደርገን ስሙ እንዲወደስ
ክብሩ እንዲቀደስ ነው።
15 ስለዚህ፥ በጌታ ያላችሁን እምነትና
ለክርስቲያኖች ያላችሁን ፍቅር፥ከሰማሁበት
ጊዜ አንሥቶ፥ 16-17 እግዚአብሔርን ከማመ
ስገን የተቆጠብኩበት ሰዓት የለም። የክብር
ባለቤት የሆነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስ
ቶስ አምላክ እግዚአብሔር፥እርሱን የበለጠ
እንድታውቁት መንፈሳዊ ማስተዋልንና ጥበ
ብን እንዲያድላችሁ ዘወትር እለምነዋለሁ።
18 እንዲሁም የተጠራችሁለት ተስፋ ምን
ያህል የከበረ መሆኑን ለማወቅ እንድት
ችሉ፥ ዓይነ ልቦናችሁን እንዲያበራላችሁ፥
የዘወትር ጸሎቴ ነው። ይህም ተስፋ እግዚ
አብሔር እንደባለጠግነቱ መጠን ለቅዱሳን
ያዘጋጀው የከበረ እርስት ነው። 19 ለምንታ
መንበት ለእኛም፥ወደር የሌለው አምላካዊ
ኃይሉ የቱን ያህል ታላቅ መሆኑን እንድታ
ውቁም፥ እጸልያለሁ። 20 እግዚአብሔርም
ክርስቶስን ከሞት አስነሥቶ በቀኙ በክብር

ባስቀመጠው ጊዜ ይህን ወደር የሌለውን
ኃይሉን በተግባር አሳይቷል። 21 እግዚአብ
ሔር ለክርስቶስ ፣ በዚህና በሚመጣውም
ዓለም ካሉት አለቆች ፣ ገዢዎች ፣ ሥልጣና
ትና ኃይላት ሁሉ በላይ እጅግ የላቀ ፣ ስምና
ግርማ ፣ ሰጥቶታል። 22 ማናቸውንም ነገር
ከእግሩ በታች አስገዝቶለታል። በቤተ ክርስ
ቲያንም ውስጥ ፣ የሁሉ ነገር ራስ አድርጎ
ሾሞታል። 23 ቤተ ክርስቲያን ፣ ሁሉ በሁሉ
የሆነው እርሱ ክርስቶስ የሚያድርባት
አካሉ ናት።

## ምዕራፍ 2

1 እናንተ ቀድሞ በበደላችሁና በኃጢአ
ታችሁ ምክንያት የሞታችሁ ነበራችሁ።
2 በዚያን ጊዜ እንደ ሌሎቹ እናንተም ኃጢ
አትን ታዘወትሩ ነበር። እንዲሁም ፣ ጌታን
የሚቃወሙትን ሰዎች ልብ ፣ በዓመፅ ለሚሞ
ላውና በአየር ላይ ገዢ ለሆነው ለሰይጣን
ፈቃድ ፣ ትታዘዙ ነበር። 3 እኛም ቀድሞ
እንደ ሥጋችን ፈቃድ እየተመላለስንና
ምኞታችንን እየፈጸምን ስሜታችንን ብቻ
በመከተል እንኖር ነበር። ከዚህም ኃጢአ
ተኛ ተፈጥሮአችን የተነሣ ፣ እኛም እንደሌ
ሎቹ አመፀኞች ከእግዚአብሔር ቁጣ ሥር
ነበርን።

4 ነገር ግን ፣ እግዚአብሔር ለምሕረቱና
ለፍቅሩ ወሰን የሌለው አምላክ በመሆኑ ፣
5 ምንም እንኳ በኃጢአታችን ምክንያት
የሞትን ብንሆንም ፣ በጸጋው ብቻ አድኖ ፣
ከሙታን ባስነሣው በክርስቶስ ሕያዋን አድ
ርጎናል። 6 እግዚአብሔር ከኢየሱስ ክርስቶስ
ጋር አስነሥቶ ፣ በሰማያዊ ሥፍራ አብሮ አስ
ቀምጦናል። 7 እግዚአብሔርም ይህን ያደረገ
ልን ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት ለሰዎች
የሰጠው እጅግ ታላቅ የሆነው ጸጋው ፣ በሚ
መጡት ዘመናት በእኛ እንዲገለጥ ፈቃዱ
ስለሆነ ነው።

8 ኢየሱስ ክርስቶስን በማመናችሁ በጸ
ጋው ድናችኋል ፤ ይህም እናንተ በራሳችሁ
ያገኛችሁት ሳይሆን ፣ የእግዚአብሔር ስጦታ
ነው። 9 መዳን ለምናደርገው መልካም ተግ
ባር ፣ የሚሰጥ ዋጋ አይደለም። ማንም ሰው ፣
'ደኅንነትን ያገኘሁት በበጎ ሥራዬ ነው'
ሊል አይገባም። 10 እግዚአብሔር ለዚህ ያበ
ቃንና በክርስቶስ አዲስ ሕይወት የሰጠን
አስቀድሞ ያዘጋጀልንን በጎ ነገር በመሥ
ራት በዘመናችን ሁሉ ስሙን እንድናከብር
ነው።

11 ከዚህ በፊት ፣ እናንተ በትውልድ አሕ
ዛብ የነበራችሁትን ፣ በሥጋ የተገረዙ አይ
ሁድ ፣ «ያልተገረዛችሁ» እያሉ ይነቅፏችሁ
እንደነበር አስታውሱ። 12 በዚያ ዘመን ከክር
ስቶስ አንድነት ርቃችሁ ፣ ከእግዚአብሔር
ሕዝብ ከእሥራኤልና ለእነርሱም ከተሰጠው
ቃል ኪዳን ውጪ ሆናችሁ ፣ በዚህ ዓለም
ያላንዳች ተስፋና ያለ እግዚአብሔር ትኖሩ
ነበር።

13 አሁን ግን ክርስቶስ ደሙን አፍስሶ
ከኃጢአታችሁ ስላዳናችሁ ፣ እናንተ በፊት
ርቃችሁ የነበራችሁት አሕዛብ ወደ እግዚአ
ብሔር ለመቅረብ በቅታችኋል።

14 ክርስቶስ ሰላማችን ነው። እርሱ እናን
ተንና ፣ እኛን አይሁዶችን ፣ የአንድ ቤተሰብ
ልጆች አድርጎናል። ያነቃቅፈን የነበረውን
ሕግና ሥርዓት በሞቱ አስወግዶ ፣ ያለያየንን
የጠብ ግድግዳ በማፍረስ ፣ በመካከላችን ሰላ
ምን መሠረተልን። 15 ከአይሁድም ከአሕዛ
ብም መርጦ ፣ ለራሱ የሚሆን አዲስ ሕዝብ
አዘጋጅቷል። 16 በመስቀል ላይ በመሞ
ቱም ፣ በመካከላችን የነበረውን ጠብ አስወ
ግዶ ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ ፣ የአ
ንድ አካል ብልቶች አድርጎናል። 17 እንዲ
ሁም በቅርብ ለነበርነው ለእኛም ሆነ ፣
በሩቅ ለነበራችሁት ለእናንተ የሰላምን ወን
ጌል ሰብኳል። 18 ከእንግዲህ አሕዛብ ወይም
አይሁድ የሚል ልዩነት በመካከላችን ሳይ
ኖር ፣ ሁላችንም በክርስቶስ ትሩፋት መሠ
ረት በመንፈስ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር
አብ ለመቅረብ ችለናል።

19 ከእንግዲህ ወዲህ እናንተ ከእግዚአብ
ሔር ቤተሰቦች ጋር አብራችሁ ዜጎች
እንጂ ፣ ባዕዶች አይደላችሁም። እንዲሁም
ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በአንድ ላይ ፣ የእ
ግዚአብሔር ወገኖች እንጂ እንግዶች አይደ
ላችሁም።

20 የሕንፃው የማዕዘን ራስ ክርስቶስ
ሲሆን ፣ እናንተም በሐዋርያትና በነቢያት
መሠረት ላይ ታንፃችኋል። 21 እኛ በክርስ
ቶስ የምናምን ሁሉ የእግዚአብሔር መቅ
ደስ ለመሆን በጌታ የምንገነባ ነን። 22 እናን
ተም እርስ በእርስ በመያያዝና በመገጣጠም
የእግዚአብሔር ማደሪያዎች ለመሆን በመን
ፈስ እየተገነባችሁ ነው።

## ምዕራፍ 3

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ የሆንኩ
እኔ ጳውሎስ ፣ ለእናንተ ለአሕዛብ የደኅንነ
ትን ወንጌል በመስበኬ ምክንያት ፣ በእሥር
ላይ እገኛለሁ። 2-3 እናንተን አሕዛብን አገለ

ግል ዘንድ ስለተቀበልኩት የእግዚአብሔር
ጸጋ መቼም ሳትሰሙ አልቀራችሁም።
ይህም ከዚህ በፊት ባጭሩ እንደጻፍኩላ
ችሁ፥እግዚአብሔር በመንፈሱ ስለገለጠልኝ
ምሥጢር ነው። 4 ይህንን በምታነብቡበት
ጊዜ፥የክርስቶስን ምሥጢር ጥልቀት ምን
ያህል እንደተረዳሁ ትገነዘባላችሁ። 5 እግዚ
አብሔር አሁን ለቅዱሳን ሐዋርያትና ነቢ
ያቱ በመንፈስ ቅዱስ የገለጠው ይህ ምሥ
ጢር፥ባለፉት ዘመናት ከነበሩ ሰዎች የተሰ
ወረ ነበር።

6 ምሥጢሩም አሕዛብ ከእሥራኤል ጋር
ወራሾች ለመሆን በወንጌል መጠራታቸውና
የአንድ አካል ክፍሎች በመሆን በክርስቶስ
ኢየሱስ አብረው የተሰፋው ተካፋዮች መሆ
ናቸው ነው። 7 እግዚአብሔር በኃይሉ በሰ
ጠን በጸጋው ስጦታ፥የዚህ ወንጌል አገል
ጋይ ሆኛለሁ።

8 ከሌሎቹ አገልጋዮቹ ሁሉ የማንስ ብሆ
ንም፥ጥልቅና ታላቅ የሆነውን የክርስቶስን
ባለጠግነት ለአሕዛብ አበሥር ዘንድ፥ይህን
ጸጋ ተቀበልኩ። 9 እንዲሁም የሁሉ ፈጣሪ
የሆነው አምላክ፥ከመጀመሪያው አንሥቶ
በምሥጢር ይዞ ያቆየውን ይህንን የደኅን
ነት እቅድ፥ለሰው ሁሉ እንዳብራራ በጸጋው
ጠራኝ።

10 ይህን ያደረገውም፥ጥልቅና ሰፊ የሆ
ነው ጥበቡ፥አሁን በቤተ ክርስቲያን አማካ
ይነት በሰማይ ለሚገኙ ሥልጣናትና ኃይ
ላት እንዲገለጽ ነው። 11 እግዚአብሔር አስ
ቀድሞ ያሰበውን ይህን የዘላለም እቅዱን፥
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከፍጻሜ አድር
ሶታል።

12 ስለዚህ እኛ በክርስቶስ ያመንነው፥ያለ
ምንም ፍርሃት በአለኝታ፥እግዚአብሔር
ፊት መቅረብ እንችላለን።

13 እንግዲህ በመታሠሬ ተስፋ አትቁ
ረጡ። ይልቁን፥እንዲህ ያለውን መከራ የም
ቀበለው ለእናንተ በመሆኑ፥እንደ ክብር
ልትቆጥሩት ይገባል። 14-15 ይህን ታላቁን
የእግዚአብሔርን እቅድና ጥበብ ሳስብ፥በሰ
ማይና በምድር ለሚኖሩ ቅዱሳን ሁሉ
አባት በሆነው በእግዚአብሔር ፊት፥በጉል
በቴ እንበረከካለሁ። 16 ጸሎቴም፥አምላክ
በታላቅ ባለጠግነቱ የሚያበረታና የሚያጸና
ችሁን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል፥እንዲሰጣ
ችሁ ነው። 17 ክርስቶስ በእምነት በልባችሁ
እንዲኖር፥እንዲሁም በጌታ ፍቅር ሥር ሰድ
ዳችሁ በእርሱ ኃይል እንድትመላለሱ፥እጸ
ልያለሁ። 18 ከሌሎች የእግዚአብሔር
ልጆች ሁሉ ጋር፥አእምሮን ሁሉ የሚያል
ፈው የክርስቶስ ፍቅር፥ከፍታውና ጥልቀቱ
ምን ያህል እንደሆነ አውቃችሁ፥ 19 በእግዚ
አብሔር ፍጹም በረከት እንድትሞሉ፥
ከልብ እጸልያለሁ።

20 ከምንመኘው፥ከምናስበው፥ተስፋ ከም
ናደርገውና ከምንለምነው እስበልጦ፥እስደ
ናቂ በሆነው ኃይሉ በሕይወታችን ውስጥ
ሊሠራ ለሚችለው ለእግዚአብሔር፥
21 በቤተ ክርስቲያን በኩል በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ስም ከትውልድ እስከ ትውልድ ክብ
ርና ምስጋና ይድረሰው። አሜን!

## ምዕራፍ 4

1 ጌታን በማገልገሌ በእሥር ላይ የምገኝ
እኔ ወንድማችሁ፥እግዚአብሔር ራሱ በጸ
ጋው የጠራችሁ በመሆኑ፥አኗኗራችሁና
አድራጎታችሁ እርሱን ደስ የሚያሰኝ ሆኖ
እንዲገኝ እለምናችኋለሁ። 2 ትሑቶችና
ገሮች በመሆን፥እርስ በእርሳችሁ በመቻ
ቻል፥በፍቅር ጸንታችሁ ኑሩ። 3 ከመንፈስ
ቅዱስ ያገኛችሁትን አንድነት፥በሰላም በመ
ኖር ለመጠበቅ ተጣጣሩ።

4 እኛ ሁላችን የአንድ አካል ብልቶች
ነን። አንድ መንፈስ ተቀብለናል። እናንተም
በተጠራችሁ ጊዜ እንደተረዳችሁት ሁላች
ንም ለአንድ ታላቅ ተስፋ ታድመናል።
5 አንድ ጌታ፥አንዲት እምነት፥አንዲትም
ጥምቀት አለን። 6 እንዲሁም ከሁሉ በላይ
የሆነ፥በሁላችንም አድሮ የሚኖር፥የሁሉ
አባት የሆነ፥አንድ አምላክ አለን። 7 ነገር
ግን፥ክርስቶስ ከተትረፈረፈ ጸጋው ለእያንዳ
ንዳችን በፈቀደው መጠን፥የተለያየ የጸጋ
ስጦታ አድሎናል።

8 «ወደ ላይ ሲወጣ፥ ብዙ ሠራዊት
ማረከ፤ለሰዎችም ስጦታን አደለ» የሚለው
የመጽሐፍ ቃል የተነገረው ስለዚህ ነው።
9 እዚህ ላይ፥ «ወደ ላይ ሲወጣ» የሚለውን
ቃል ልብ ብሎ መመልከት ይገባል። ይህ
ቃል ክርስቶስ ወደ ምድር ጥልቅ የወረደ
መሆኑን ያስረዳናል። 10 በሌላም በኩል
ደግሞ፥ወደ ሰማይ የወጣው፥ቀድሞ ከሰማይ
ወደዚች ምድር ወርዶ የነበረው፥ራሱ ክርስ
ቶስ ነው። እርሱ በሁሉ ቦታ የሚገኝና
ሁሉንም የሚሞላ ነው።

11 ክርስቶስ፥አንዳንዶችን ሐዋርያት፥አን
ዳንዶችን ነቢያት፥አንዳንዶችን ወንጌል ሰባ
ኪዎች፥አንዳንዶችን ደግሞ የምዕመናን እረ
ኞችና መምህራን አድርጎ በቤተ ክርስቲያን
አኑሮአል።

12 እነዚህን አገልጋዮች ያኖራቸውም ፥
የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን
ታድግና ትገነባ ዘንድ ምዕመናንን ለመንፈ
ሳዊ አገልግሎት እንዲያዘጋጁ ነው።
13 ከዚህ የተነሣም ሁላችንም፥ስለ እግዚአብ
ሔር ልጅ ስለ ክርስቶስ ባለን እምነትና
ዕውቀት ፥ ፍጹም ብስለትና አንድነት ይኖረ
ናል። ክርስቶስንም ለመምሰልና ከፍጹምነ
ቱም ለመካፈል እያደግን እንሄዳለን።
14 ከእንግዲህ ወዲህ ፥ ሐሰቱን እውነት
አስመስሎ በማቅረብ ፥ ማንም ሰው እንደ
ሕፃን ሊያታልለን አይገባም። በተንኰለኞች
ሰዎች የሐሰት ትምህርት በመታለል ግራ
ልንጋባም አያስፈልግም። 15-16 በዚህ ፈንታ
ግን እውነትን ከፍቅር ጋር አዋሕደን፥ወደ
ፊት ልንራመድ ያስፈልጋል። እውነትን እየ
ተናገርንና በእውነት እያገለገልን፥የቤተ ክር
ስቲያን ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል
እናድጋለን። በእርሱም አማካይነት ፥የአካሉ
ብልቶች የሆኑ ምዕመናን በፍጹም አንድ
ነት ተያይዘው፥ለእያንዳንዱ በተሰጠው ጸጋ
መሠረት በመደጋገፍ በፍቅር ያድጋሉ።
17-18 በጌታ ይህንን ላሳስባችሁ እፈልጋ
ለሁ። በመንፈስ አዲስ ልደትን ያላገኙ
ሰዎች ግራ የተጋቡና ዓይናቸው የታወረ
ስለሆነ ፥ እነርሱን አትምሰሉዋቸው። ልባ
ቸው ከመደንደኑና በጨለማ ውስጥ ከመኖ
ራቸው የተነሣ፥ከእግዚአብሔር የራቁና ስለ
እነርሱ የሚነገረውንም የማያስተውሉ
ናቸው። 19 ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን
ነገር ለመለየት ፥ ግድ የሌላቸውና ራሳቸው
ንም ለርኩሰት አሳልፈው የሰጡ ጉስቋሎች
ናቸው። ከፉ ምኞት ይዞ ስለሚነዳቸው ፥
አስጸያፊ ለሆነ የብልግና ተግባር ተገዢዎች
ይሆናሉ።
20 እናንተ ግን ፥ ክርስቶስን የተረዳችሁት
በእንዲህ ያለ መንገድ አይደለም። 21 በእር
ግጥ ቃሉን የሰማችሁና ስለ እርሱም የተነገ
ረውን እውነት የተቀበላችሁ ከሆነ፥ 22 ያን
የበሰበሰና የረከሰ የቀድሞ አኗኗራችሁን ፥
ወዲያ አሽቀንጥራችሁ ጣሉት።
23 ከእንግዲህ ወዲህ ያለው ሕይወታ
ችሁ ፥ ከቀድሞው የተለየና በመንፈስ ኃይል
የተለወጠ ይሁን። 24 በእውነተኛው ጽድ
ቅና ቅድስና ፥ እግዚአብሔርን ለመምሰል
የተፈጠረውን አዲሱን ሰውነት ልበሱ።
25 እናንተ አንድ አካል አንድ አምሳል
ስለ ሆናችሁ፥አንዱ ለሌላው አይዋሽ፤አንዱ
ለሌላው የሚዋሽ ከሆነ የምትጐዱት ራሳች
ሁን ነውና ፥ እውነቱን ብቻ ተናገሩ።
26-27 የሚያስቆጣ ነገር ገጥሟችሁ ለጊዜው
ቢያናድዳችሁ እንኳ ፥ቁጣችሁን አውላችሁ
በማሳደር ለሰይጣን እድል አትስጡት።
28 ከዚህ ቀደም የመስረቅ ልማድ የነበ
ረው ፥ ከእንግዲህ ወዲህ መስረቁን ይተው።
ለወደፊቱ ግን በገዛ እጁ እየሠራ ራሱንም
ሌሎች ችግረኞችንም ይርዳ። 29 ከአንደበታ
ችሁ ክፉ አይውጣ። ንግግራችሁ በጎ ነገርን
የተሞላ ፥ ሰዎችን የሚያንጽና የሚጠቅም
ይሁን።
30 ለመጨረሻው የደኅንነት ቀን የታተማ
ችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ
አታሳዝኑት።
31 ቂም በቀልን ፥ ቁጣን ፥ ጩኸትን ፥ ስድ
ብን ፥ ጥላቻንና ጠብን ፥ ከእናንተ አስወግዱ።
32 እርስ በእርሳችሁ ደጎችና ርኅሩሆች
ሁኑ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳ
ላችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባ
ባሉ።

## ምዕራፍ 5

1 የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች
በመሆናችሁ በማናቸውም ነገር የእርሱን
ምሳሌ ተከተሉ። 2 ክርስቶስ እንደወደደንና
ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ስጦታና
ጣፋጭ መዓዛ ያለው መስዋዕት አድርጎ
በእኛ ፈንታ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ፥እናን
ተም የእርሱን አርአያ በመከተል ፥ ለሰዎች
ሁሉ ፍቅር ይኑራችሁ።
3 የቅዱሳንን ስም የሚያረክስ ማናቸው
ንም ዓይነት ቅንዝረኝነት ፥ የርኩሰት ተግባ
ርና ስስት የሚፈጽም ፥ በመካከላችሁ አይ
ኑር። ይህን የመሰለ ነውረኛ ተግባር ይፈጽ
ማሉ ተብሎ ስማችሁ በክፉ እንዳይነሣ
ተጠንቀቁ። 4 ማንኛውም ዓይነት የብልግና
ንግግርና ዋዛ ፈዛዛ፥ከእናንተ ይራቅ። በዚህ
ፈንታ ግን የእግዚአብሔርን በጎነት በማሰብ
ምስጋና አቅርቡ።
5 አመንዝሮች ወይም ርኩስ ተግባር የሚ
ፈጽሙ ፥ ወይም ማንኛውም ጣዖትን የሚያ
መልክ ሰው ፥ በክርስቶስና በእግዚአብሔር
መንግሥት ዕጣ ክፍል እንደሌለው እርግጠ
ኞች ሁኑ። 6-7 ይህን የመሰለውን አስነዋሪ
ተግባር መፈጸም ፥ ጉዳት የሌለበት አስመስ
ለው አጣፍጠው በመናገር ከሚከራከሩ
ሰዎች ፥ ተጠንቀቁ። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች
ከእግዚአብሔር ቁጣ ስለማያመልጡ አትተ
ባበሩዋቸው። 8 ከዚህ ቀደም በጨለማ
ውስጥ የምትኖሩ ቢሆንም ፥ ዛሬ ግን ጌታን
በማወቃችሁ በብርሃን ሆናችኋል። 9 ብርሃ

ኑም በልቦናችሁ ውስጥ የበራ በመሆኑ የበጎ
ነትን፣የጽድቅንና የእውነትን ተግባር እየፈ
ጸማችሁ እንደብርሃን ልጆች ኑሩ።
10 እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትም ተጣ
ጣሩ። 11 ፍሬቢስ ከሆነ ከጨለማ ሥራ ጋር
አትተባበሩ። ርካሽ የሆነ ክፉ ሥራቸውንም
በይፋ አውግዙ። 12 በክርስቶስ የማያምኑ
ሰዎች፣ በጨለማ ተሰውረው የሚፈጽሟቸ
ውን የረከሱ ሥራዎች፣ 'እንዲህ ነው' ብሎ
መናገሩ እንኳን ያሳፍራል። 13 ነገር ግን
ለብርሃን የተጋለጠ ማንኛውም ነገር እውነ
ተኛ መልኩ ቁልጭ ብሎ ይታያል።
14 ምክንያቱም ብርሃን ማንኛውንም ነገር
ጥርት አድርጎ ያሳያል። «አንተ የምትተኛ
ንቃ፤ከሞትም ተነሣ፤ክርስቶስም ያበራልሃ
ልና» የተባለውም ስለዚህ ነው።
15-16 ከዚህ የተነሣም፣ የምታደርጉትን
ሁሉ ተጠንቅቃችሁ አድርጉ። ጥበበኞችና
አስተዋዮችም ሁኑ። ዘመኑ የከፋ በመሆኑ፣
በጎ ሥራ ለመሥራት በሚያጋጥማችሁ
ዕድል ሁሉ ተጠቀሙ። 17 አለማስተዋልን
ከእናንተ አስወግዳችሁ፣የጌታን ፈቃድ ለማ
ወቅ ተጣጣሩ። 18 ብርቱ ጉዳት የሚያስከ
ትለውን የወይን ጠጅ በመጠጣት አትስ
ከሩ። በዚህ ፈንታ ግን ለክርስቲያን እንደ
ሚገባ ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ
ችሁ ሁኑ።
19 አንድ ላይ በምትሆኑበት ጊዜ፣በመዝ
ሙርና በምስጋና ጌታን እያወደሳችሁ እርስ
በእርስ ተጽናኑ። 20 አምላካችንና አባታችን
ለሆነው እግዚአብሔር፣በጌታችን በኢየሱስ
ስም፣ ስለ ማንኛውም ነገር አዘውትራችሁ
ምስጋና አቅርቡለት።
21 አንዱ ለሌላው ራሱን በማስገዛት፣ለክ
ርስቶስ ያላችሁ አክብሮት በመካከላችሁ
ይገለጥ። 22 ሚስቶች ሆይ፣ለጌታ እንደምት
ታዘዙ ለባሎቻችሁም ታዘዙ። 23 ክርስቶስ
ለአካሉ ለቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነ፣
ባልም የሚስቱ ራስ ነው። 24 ስለዚህ፣ቤተ
ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትታዘዝ፣ሚስ
ቶችም በማናቸውም ነገር ለባሎቻቸው
ይታዘዙላቸው።
25 ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ራሱን ለሞት
አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ ቤተ ክርስቲ
ያንን እንደወደዳት፣ እናንተም ሚስቶቻች
ሁን ውደዱ። 26 ክርስቶስ ይህን ያደረገው፣
ቤተ ክርስቲያን በውኃና በቃሉ ነጽታ ቅድ
ስት እንድትሆን ሲሆን፣ 27 እንደዚሁም፣
ነውርና ነቀፋ የማይገኝባት ንጽሕትና ቅድ
ስት ሆና በፊቱ እንድትቀርብ ነው። 28 ባሎ
ችም፣ ሚስቶቻቸውን እንደራሳቸው አድር
ገው መውደድ አለባቸው። ባል ሚስቱን
ሲያፈቅር ልክ ራሱን እንዳፈቀረ ይቆጠ
ራል። 29-30 ክርስቶስ አካሉ የሆነችውን
ቤተክርስቲያን እንደሚንከባከባት፣ አስፈላጊ
ውን ምግብ እየመገበ ይንከባከበዋል እንጂ፣
ማንም የገዛ አካሉን አይጠላም። እኛም የክ
ርስቶስ የአካሉ ብልቶች ነን።
31 «ከዚህም የተነሣ፣ወንድ አባትና እና
ቱን ይተዋል። ከሚስቱም ጋር ይዋሐዳል።
ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ።» 32 ይህ
ጉዳይ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ምሥጢር
የያዘ ቢሆንም፣ክርስቶስንና ቤተክርስቲያንን
የሚመለከት በመሆኑ፣እዚህ ላይ አንሥቼዋ
ለሁ።
33 ስለዚህ፣ባል ሚስቱን እንደ ራሱ አድ
ርጎ መውደድ ይገባዋል። ሚስትም ለባሏ
ተገቢውን ክብር የምትሰጠው መሆን አለ
ባት።

## ምዕራፍ 6

1 ልጆች ሆይ፣ተገቢ ነገር በመሆኑ ለወላ
ጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ። 2-3 «አባትህንና እና
ትህን አክብር» የሚለው ትእዛዝ፣ከአሥርቱ
ትእዛዛት መካከል የተስፋ ቃል ያለበት የመ
ጀመሪያው ትእዛዝ ነው። ተስፋውም፣
«በምድር ላይ ዕድሜህ ይረዝማል፣ኑሮህም
ይሳካል» ይላል።
4 አባቶች ሆይ፣ ልጆቻችሁን በፍቅርና
በምክር እያረማችሁ የጌታን መንገድ እንዲ
ከተሉ አሳድጓቸው እንጂ፣በመቆጣትና በማ
በሳጨት እንዲመረሩ አታድርጓቸው።
5 አገልጋዮች ሆይ፣ለክርስቶስ እንደመታ
ዘዝ ያህል ነውና ምድራዊ አሳዳሪዎቻችሁን
በፍርሃትና በቅን ልቡና ታዘዟቸው።
6-7 የምታገለግሏቸውም እነርሱ ሲኖሩ ሽር
ጉድ በማለት፣እነርሱ ዞር ሲሉ ግን በመለገ
ምና ቸል በማለት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር
የሚወደው በመሆኑ፣እንደ ክርስቶስ አገልጋ
ዮች በደስታና በሙሉ ልብ አገልግሏቸው።
8 ተገዢም ሆነ ነጻ ዜጋ፣ከልቡ ለሚሠራው
ጥሩ ሥራ፣ ከጌታ ወሮታውን የሚቀበል
መሆኑን አትዘንጉ።
9 እናንተ አሳዳሪዎች፣ዛቻን ሁሉ አስወግ
ዳችሁ አገልጋዮቻችሁን በቅንነት አስተዳ
ድሩ። በሰማይ እናንተንም ሆነ እነርሱን
የሚመለከት፣ ጌታ እንዳለና እርሱም የሰው
ፊት አይቶ እንደማያደላ አትዘንጉ።
10 በመጨረሻም፣በጌታ ኃይልና ብርታት
የጸናችሁ ሁኑ። 11 የሰይጣንን ተንኰል

መቋቋም እንድትችሉ ፥ የእግዚአብሔርን
ሙሉ የጦር ትጥቅ ልበሱ። 12 የምንዋጋው
ሰብአዊ ፍጡራን ከሆኑ ሰዎች ጋር ሳይ
ሆን፥ይህንን የጨለማ ዓለም ከሚያስተዳድሩ
መንፈሳውያን ገዢዎችና ኃይላት ፥ እንዲ
ሁም ሥልጣናትና በአየር ላይ ከነኑ የርኩ
ሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው።
13 ስለዚህ፥የእግዚአብሔርን የጦር መሣ
ሪያ አሁኑኑ ታጠቁ። ምክንያቱም ክፉው
ቀን ሲመጣ፥ወደ ኋላ ሳታፈገፍጉ የጠላትን
ጥቃት ለመመለስና በመጨረሻም በድል
ለመቆም ያስችላችኋልና።
14 የእውነትን ቀበቶ ታጥቃችሁ፥የጽድ
ቅን ጥሩር አጥልቃችሁ፥ 15 የሰላምን ወን
ጌል ተጫምታችሁ ፥ 16 የሚንቀለቀለውን
የሰይጣንን ፍላጻ የምትመክቱበትን የእም
ነት ጋሻ አንግባችሁ፥ 17 የደኅንነትን ራስ
ቁር በራሳችሁ ላይ ደፍታችሁ፥የእግዚአብ
ሔርን ቃል እንደ መንፈስ ሰይፍ ጨብጣ
ችሁ ዝግጁ ሆናችሁ ቁሙ።
18 ምን ጊዜም በጸሎት ትጉ። የሚያስፈ
ልጋችሁን አሟልቶ እንዲሰጣችሁ፥መንፈስ
ቅዱስ በሚመራችሁ መንገድ ዘወትር እግዚ
አብሔርን ለምኑት። ለቅዱሳን ሁሉ ፥ ያለ
መሰልቸት ጸልዩ። 19 የወንጌሉን ቃል ለመ
ስበክ ዕድል እንዳገኝና፥እንደበቴም ተከፍቶ
ምሥጢሩን ያለ ፍርሃት አብራርቼ መግለጽ
እንድችል ፥ ለእኔም ጸልዩልኝ። 20 ይህንኑ
የወንጌል ቃል በማስተማሬ፥በሰንሰለት የታ
ሠረ የጌታ አምባሳደር ሆኛለሁ። ስለዚህ፥
የሚገባኝን ያህል ያለ ፍርሃት መመስከር
እንድችል፥ጸልዩልኝ። 21 በጌታ የተወደደው
ወንድማችንና፥ወንጌልን በማስተማር ታማኝ
ረዳታችን የሆነው ቲኪቆስ፥ስለ እኔ ሁኔታ
በሰፊው ያጫውታችኋል። 22 ወደ እናንተ
የምልከውም፥ስለ እኛ ሁኔታ ማናቸውንም
ነገር በይበልጥ ለማወቅ እንድትችሉና እን
ድትጽናኑ ነው።
23 እምነት የተሞላበት ሰላምና ፍቅር፥
ከእግዚአብሔር አብና ከጌታችን ከኢየሱስ
ክርስቶስ፥ለወንድሞች ሁሉ ይድረሳቸው።
24 ጸጋና የዘላለም ሕይወት፥ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስን ከሚወዱ ሁሉ ጋር ይሁን።

የናንተው
ጳውሎስ

## ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለፊልጵስዩስ ሰዎች የጻፈው መልእክት

### መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን፥የተጻፈበትም ዘመን በ63 ዓ.ም. ገደማ እንደሆነ ይገመታል። የተጻፈበት ምክንያት ምዕመናን በክርስቶስ አማካይነት የሚያገኙትን የሕይወት ደስታ ለማሳሰብ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን ወንጌል በማስተማሩ ምክንያት ታሥሮ ነበር። ሆኖም መታሠሩን በደስታ ተቀበለው እንጂ አላዘነበትም። ስለዚህ ክርስቲያኖች የመጣው ቢመጣ፥አንድነታቸውን አጽንተው፥መንፈሳዊ ሕይወታቸውን አጠንክረውና በመልካም ባሕርይ ታንጸው፥በሰላምና በደስታ እንዲኖሩ በዚህ መልእክት ያሳስባቸዋል።

---

## ምዕራፍ 1

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች ከሆኑት
ከጳውሎስና ከጢሞቴዎስ ፤ በፊልጵስዩስ
ከተማ ለምትገኙ ምዕመናን ሁሉ ፥ የቤተ
ክርስቲያን መሪዎችና ዲያቆናት።
2 ከእግዚአብሔር ከአባታችንና ከጌታችን
ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ጸጋና ሰላም ይብዛ
ላችሁ።
3 እናንተን ባስታወስኩ ቁጥር እግዚአብ
ሔርን አመሰግነዋለሁ ፤ 4 ስለእናንተም ዘወ
ትር ስጸልይ ደስ እያለኝ ነው። 5 ምክንያ
ቱም የምሥራቹን ቃል ከሰማችሁበት ጊዜ
አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ፥ይህ የክርስቶስ
የምሥራች ቃል ለሰው ሁሉ እንዲዳረስ፥በበ
ኩላችሁ የሚገባውን ጥረት አድርጋችኋ
ልና። 6 በሕይወታችሁ መልካም ሥራን
መሥራት የጀመረው እግዚአብሔር፥ኢየሱስ

ክርስቶስ እስከሚመጣበት ቀን ድረስ ይህንኑ
መልካም ሥራ ከፍጻሜ ያደርሰዋል።
7 ለእናንተ ያለኝ ስሜት የተለየ ነው።
ከታሠርኩ በኋላም ሆነ ከዚያ በፊት ፣ ስለ
እውነት እየመሰከርኩ ስለ ክርስቶስ በምሰብ
ክበት ጊዜ፣ሁላችሁም የእግዚአብሔርን የአ
ገልግሎት ጸጋ አብራችሁ ተካፍላችኋል።
ስለ እናንተ እንዲህ አጥብቄ የማስበውም
ስለዚህ ነው። 8 ምን ያህል እንደምናፍቃች
ሁና በጌታ ፍቅር እንደምወዳችሁ የልቤን
የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። 9 ልባ
ችሁ በፍቅር እንዲሞላና ሰዎችን እንድት
ወዱ ፣ በመንፈሳዊ ዕውቀትም እንድትበስሉ
እጸልያለሁ። 10 እንዲሁም ፣ ክፉውን ከደጉ
እንድትለዩና ምንም ዓይነት ነቀፋ ሳይገኝባ
ችሁ ክርስቶስ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ ፣
ያለ ነውር እንድትኖሩ እጸልይላችኋለሁ።
11 በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘው የጽድቅ
ፍሬ ሕይወታችሁን ሲሞላ እግዚአብሔርም
በዚሁ ይከበራል።
12 ወንድሞቼ ሆይ ፣ የደረሰብኝ መከራ
ሁሉ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን የምሥራች
ቃል ለሰዎች ለማዳረስ እድል ሰጥቶኛል።
13 የታሠርኩት ወንጌል ተገኝቶብኝ ሳይ
ሆን ፣ ክርስቶስን በማመኔ መሆኑን ፣ እዚህ
አብረውኝ ያሉት እሥረኞች ፣ የሚጠብቁን
ዘቦችና ሌሎችም ሰዎች ሁሉ በደንብ ተረ
ድተውታል። 14 እኔ ከታሠርኩ ወዲህም
ብዙ ክርስቲያኖች እሥራትን ከምንም ሳይ
ቆጥሩ በእምነታቸው በርትተዋል። ስለ ክር
ስቶስም በድፍረት መመስከር ይዘዋል።
15 ነገር ግን፣አንዳንዶች የክርስቶስን የም
ሥራች ቃል የሚሰብኩት በእኔ ቀንተው
ነው። አንዳንዶችም የሚሰብኩት ሁከትና
መለያየት ለመፍጠር ነው። በሌላ በኩል
ደግሞ ፣ በንጹሕ መንፈስ የምሥራቹን ቃል
የሚሰብኩም አሉ። 16-17 አንዳንዶቹ የምሥ
ራቹን ቃል በንጹሕ መንፈስ የሚሰብኩት
እኔን ስለሚወዱ ነው። እዚህ በእሥራት
ላይ ያለሁት ወንጌልን በማስተማሬ ምክን
ያት እንደሆነ ያውቃሉና። የቀሩት ግን ክር
ስቶስን የሚሰብኩት ፣ በቅንነት ሳይሆን በቅ
ናት ተነሳስተው እሥራቴን ለማክበድ ነው።
18 እኔ ግን ዓላማቸው ምንም ይሁን ምን ፣
የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች ቃል
በመሰበኩ ብቻ ደስ ይለኛል።
19 የእናንተ ጸሎትና የመንፈስ ቅዱስ
እርዳታ ይህን ያለሁበትን ሁኔታ ለመዳኔ
እንደሚያደርግልኝ ስለማውቅ ፣ ደስታዬ አይ
ቋረጥም። 20 በምንም ዓይነት መንገድ እንደ
ማላፍር እርግጠኛ ነኝ። መከራ ቢያሳዩኝም
እንኳ ፣ ስለ ጌታ መመስከሬን አልተውም።
ዋናው ምኞቴ ብሞትም ፣ ብኖርም ጌታ
በእኔ ሕይወት እንዲከብር ነው። 21 ለእኔ
በሕይወት መኖር ማለት ክርስቶስን ማገል
ገል ማለት ነው። መሞት ደግሞ ፣ እንዲያ
ውም ለእኔ የተሻለ ነገር ነው። 22 በሕይ
ወት መኖሬ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር
ለማስታረቅ የሚያስችለኝ ከሆነ ግን ፣ ከመ
ሞት ወይም ከመኖር የቱ እንደሚሻል
መምረጥ ያስቸግረኛል። 23 አንዳንድ ጊዜ
በሕይወት መኖርን እመርጣለሁ። አንዳንዴ
ደግሞ ፣ እጅግ የሚመረጥ ነውና ሞቼ ከክር
ስቶስ ጋር አብሮ መሆንን እናፍቃለሁ።
24 ይሁን እንጂ የማውቀው አንድ ነገር አለ፤
ይህም በሕይወት መኖሬ ለእናንተ ብዙ
የሚጠቅም መሆኑን ነው።
25 በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ እንድታድ
ጉና ፣ በእምነታችሁም ደስ እንዲላችሁ ልረ
ዳችሁ እንድችል ፣ እግዚአብሔር ዕድሜዬን
እንደሚያረዝመው እርግጠኛ ነኝ። 26 እንደ
ገና ተመልሼ ከእናንተ ጋር በምሆንበት
ጊዜ ፣ በደስታ ተሞልታችሁ ስለ እኔ ኢየሱስ
ክርስቶስን ለማመስገን እድል ታገኛላችሁ።
27 እኔ ተመልሼ መጥቼ ዓይናችሁን ለማ
የት ብችልም ባልችልም ፣ ለወንጌል እውነት
በአንድ ልብ እየተጋደላችሁ በእምነታችሁ
ጽኑ። ሕይወታችሁንም በክርስቶስ ኢየሱስ
ወንጌል መሠረት ምሩት። 28 በምንም ምክ
ንያት ቢሆን የሚቃወሟችሁን አትፍሩ።
ይህ ተቃውሞአቸው የሚያሳየው የእነርሱ
ጥፋት መቃረቡን ሲሆን ፣ ለእናንተ ደግሞ
ጌታ ከእናንተ ጋር እንደ ሆነና የዘላለምን
ሕይወት እንደ ሰጣችሁ ነው። 29 የተጠራች
ሁት በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ፣
ስለ እርሱም መከራን እንድትቀበሉ ጭምር
ነው። 30 እናንተ ባሁኑ ጊዜ የምትቀበሉት
መከራ ፣ ከዚህ ቀደም እኔ ስለጌታ የተቀበል
ኩትንና አሁንም በመቀበል ላይ ያለሁትን
መከራ የሚመስል ነው።

## ምዕራፍ 2

1 በክርስቶስ ያገኛችሁት ሕይወት ያበረ
ታችኋልን? ፍቅሩስ መጽናናትን ይሰጣችኋ
ልን? ከመንፈስ ቅዱስስ ጋር ሕብረት አላች
ሁን? አንዳችሁ ለሌላው ርኅራኄ ታሳያላ
ችሁ? 2 ይህ ከሆነ እርስ በእርሳችሁ ለአንድ
አሳብና ዓላማ የቆማችሁ ሁኑ። በስምምነት
ስትኖሩና በሕብረት ስታገለግሉ ማየት ደስ
ያሰኘኛል።

3 ራስን መውደድ እንዳያጠቃችሁ ተጠን
ቀቁ። የምትሠሩትን ነገር ለዝና ስትሉ አት
ሥሩ። ከእናንተ የተሻሉ ሌሎች ሰዎች
መኖራቸውንም በትሕትና ተቀበሉ። 4 ለራሳ
ችሁ የሚጠቅመውን ብቻ ከማሰብ ይልቅ፥
ሌሎችን ሊጠቅም ስለሚችል ነገር አስቡ።
5 በኢየሱስ ክርስቶስ የነበረው ይህ አስተ
ሳሰብ በእናንተም ይኑር። 6 እርሱ በባሕርዩ
አምላክ ሆኖ ሳለ የአምላክነት መብቱን
ሙጭጭ አድርጎ አልያዘም። 7 ክብሩን
ሁሉ ወደ ጎን በመተው የአገልጋይን መልክ
ይዞ በሰው አምሳል መጣ። 8 ወንጀለኞች
ይቀጡበት በነበረው መስቀል ላይ እስከመ
ሞት ድረስ ራሱን በማዋረድ ለእግዚአብ
ሔር ታዘዘ።
9 ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ ከፍ
አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን
ስም ሰጠው። 10 ይህም በሰማይ ሆነ በም
ድር፥ከምድርም በታች፥ጉልበት ሁሉ ለኢየ
ሱስ ስም እንዲንበረከክና ፥ 11 ምላስም
ሁሉ ፥ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ
ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ እንዲመሰክር ነው።
12 ወዳጆቼ ሆይ ፥ አብሬአችሁ በነበርኩ
በት ጊዜ የሰጠኋችሁን ምክር ተቀብላችሁ
በሥራ ላይ ታውሉት ነበር። በአካል ከእና
ንተ ብርቅም፥ምክሬን እንደምትከተሉ አው
ቃለሁ። እንግዲህ ደኅንነትን ስላገኛችሁ ፥
በቅዱስ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ለእግዚአብ
ሔር እየታዘዛችሁ ፥ ግራ ቀኝ ሳትሉ ወደ
ደኅንነታችሁ ግብ አምሩ። 13 እርሱን ደስ
የሚያሰኘውን ነገር እንድትመኙና በሥራም
ላይ እንድታውሉት በውስጣችሁ የሚሠ
ራው ራሱ እግዚአብሔር ነው።
14 በምታደርጉት ነገር ሁሉ ከማጉረምረ
ምና ከመከራከር ተቆጠቡ። 15 ይህንንም
የምለው፥የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆ
ናችሁ መጠን ማንም ሊነቅፋችሁ የሚችል
በት ምክንያት እንዳያገኝ ነው። ክፉ ሰዎች
በሞሉበት በዚህ ዓለም ፥ የሕይወትን ቃል
እያበሠራችሁ እንደ ብርሃን ፋና አብሩ።
16 ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ፥ በእናንተ
መካከል የፈጸምኩት አገልግሎት ፍሬ በማ
ፍራቱ ፥ ምንኛ ደስ ይለኝ ይሆን? 17 በእና
ንተ የእምነት መሥዋዕት ላይ ተጨምሮ
ደሜ እንደ ጉርፍ ቢፈስስ እንኳን ከሁላ
ችሁ ጋር አብሮ ደስ ይለኛል። 18 እንደዚ
ሁም፥እናንተም ከእኔ ጋር በዚህ ደስ ሊላ
ችሁ ይገባል።
19-20 የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ፥
ጢሞቴዎስን በቅርቡ ወደ እናንተ እልከዋ
ለሁ። እርሱ ካያችሁ በኋላ ወደ እኔ ሲመ
ለስ እንዴት እንዳላችሁ ያስረዳኛል። እኔም
ያላችሁበትን ሁኔታ ስሰማ ደስ እንደሚለኝ
እርግጠኛ ነኝ። እንደ ጢሞቴዎስ ስለ እና
ንተ የሚያስብና የሚጨነቅ ማንም ሰው የለ
ኝም። 21 ሁሉም የሚያስቡትና የሚጨነ
ቁት ስለ ራሳቸው ጉዳይ ብቻ እንጂ ስለጌታ
አገልግሎት አይደለም። 22 ጢሞቴዎስ ግን
እንዲህ አይደለም፤ልክ እንደ ልጅ ሆኖ እን
ዳገለገለኝና የክርስቶስን የምሥራች ቃል
በመስበክ ማንነቱን እንዳስመሰከረ ፥ እናን
ተም ራሳችሁ ታውቃላችሁ። 23 የእኔ ጉዳይ
ቁርጡ ሲታወቅ በቶሎ ወደ እናንተ እልከ
ዋለሁ። 24 እንዲያውም እኔም ራሴ በቅርቡ
መጥቼ ላያችሁ እንደምችል በጌታ ተስፋ
አደርጋለሁ።
25 እንዲረዳኝና እንዲደግፈኝ አስባችሁ
የላካችሁትን ወንድማችንን አፍሮዲጡን ፥
በቶሎ መልሼ ወደ እናንተ እሰድደዋለሁ።
አፍሮዲጡ እንዴት ያለ ወዳጄ መሰላችሁ?
እርሱና እኔ አብረን በአንድ ላይ ብዙ አገል
ግለናል። 26 አሁን ግን የእናንተ ናፍቆት
ይዞታል። በተለይም እንደ ታመመ የሰማ
ችሁ መሆኑን በማወቁ፥ይጨነቃሉ በማለት
በጣም ያስባል። 27 በእርግጥም በጣም
አሞት ለሞት ተቃርቦ ነበር። ጌታ ግን ለእ
ኔም ለእርሱም ሲል ማረው። ይህ ባይሆን
ኖሮ በዚህ መከራዬ ላይ የባሰ ኀዘን ይገጥ
መኝ ነበር።
28 አሁን ግን ወደ እናንተ እንዲመለስ
ወስኛለሁ። ፊቱን በምታዩ ጊዜ ምን ያህል
ደስ እንደሚላችሁና ጌታን እንደምታመሰግ
ኑት ይሰማኛል። እናንተን ደስ ሲላችሁ የእ
ኔም ሥጋት ቀለል ይላል። 29 እንግዲህ
ሲመጣ በታላቅ ደስታ በጌታ ተቀበሉት።
እንደርሱ ያሉትንም አገልጋዮች ሁሉ አክ
ብሯቸው። 30 እርሱ ለጌታ ሥራ ነፍሱን
እንኳ አሳልፎ የሰጠ ነው። እናንተ በአጠ
ገቤ ስለሌላችሁ ልታደርጉልኝ ያልቻላችሁ
ትን ሁሉ አድርጎልኛል።

## ምዕራፍ 3

1 በመጨረሻም ፥ ወንድሞቼ ሆይ በጌታ
ደስ ይበላችሁ። እንድትጠነቀቁ ይረዳችኋ
ልና አንድን ነገር ደግሜ ደጋግሜ ብጽፍላ
ችሁ አይሰለቸኝም።
2 «ለመዳን የግድ መገረዝ አለባችሁ»
ከሚሉአችሁ ውሾች ከሆኑ ከእነዚያ ክፉ
ሰዎች ተጠንቀቁ። 3 የእግዚአብሔር ልጆች
መሆናችን የሚታወቀው አካላችንን በስለት

በመቁረጥ ሳይሆን ፥ እግዚአብሔርን በመን
ፈስ በማምለክ ነው። እውነተኛው ግዝረ
ትም ይኸው ነው። እኛ ክርስቲያኖች ልን
መካ የምንችለው ክርስቶስ ለእኛ ሲል በው
ራልን የጽድቅ ሥራ እንጂ፥በራሳችን ኃይል
አይደለም።
[4]ራሱን ማዳን የሚችል መስሎት የሚ
መካ እንደ እኔ ማንም አልነበረም። ውጫዊ
በሆነው ሥርዓት የሚመካ ሰው ካለ እኔ
እበልጠዋለሁ። [5]በተወለድኩ በስምንተኛው
ቀን እንደ አይሁድ ሥርዓት ተገርዣለሁ።
የተወለድኩትም፥ከእሥራኤል ዘር ከብንያም
ወገን ነው። ንጹሕ ዕብራዊ ከመሆኔም
ሌላ ፥ ለሥርዓታቸው ቀናተኞች ከነበሩት
ፈሪሳውያን አንዱ ነበርኩ። [6]በሕግ በሚገ
ኘው ጽድቅ ረገድ ብቁ የሆንኩ ነበርኩ።
ለሃይማኖቴ ሥርዓት ከነበረኝ ከፍተኛ ቅን
ዓት የተነሣም። ክርስቲያኖችን አሳድጄአ
ለሁ። [7]ነገር ግን ከዚህ በፊት ጠቃሚ ይመ
ስለኝ የነበረውን ሁሉ ፥ አሁን ስለ ክርስቶስ
ስል ዋጋ እንደሌለውና እንደከንቱ ነገር እቆ
ጥረዋለሁ፤ከእንግዲህ ተስፋዬና እምነቴ በክ
ርስቶስ ብቻ ነው። [8]ከሁሉ የሚበልጠውን
ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታዬ በማወቅ
ብቻ ፥ ያለ ምንም ዋጋ ካገኘሁት ታላቅ
ጥቅም ጋር ሳወዳድረው፥የምመካበትን ሁሉ
እንደ ፋይዳ ቢስ ነገር እቆጥራለሁ። ክርስቶ
ስን ለሕይወቴ አትርፍ ዘንድ ሌላውን ሁሉ
ትቼአለሁ። [9]አሁን ከክርስቶስ ጋር ሕብረት
አለኝ። ደኅንነትን ያገኘሁት የኦሪትን ሕግ
በመጠበቄ ወይም ጥሩ ሰው በመሆኔ ሳይ
ሆን፥እግዚአብሔር የላከውን ክርስቶስን በማ
መን ነው። [10]ክርስቶስንና የትንሣኤውን
ኃይል በይበልጥ ለማወቅ ፥ እንደ እርሱ
መከራ ለመቀበልና በሞቱም እርሱን ለመም
ሰል ከልብ እመኛለሁ። [11]ከሞትኩ በኋላም
እንደ ገና በሕይወት ሊያኖረኝ እንደሚያስነ
ሣኝም እተማመንበታለሁ።
[12]አሁን ፍጹም ነኝ ለማለት አልች
ልም። ገና ያልደረስኩበት ብዙ ነገር
አለ። ቢሆንም ጌታ ለአገልግሎቱ ሲጠራኝ
ያቀደልኝን ነገር በሙሉ ለመቀዳጀት፥የተ
ቻለኝን ያህል እጣጣራለሁ። [13]ወንድሞቼ
ሆይ፥መሆን የሚገባኝን ገና ሆኜ እንዳልተገ
ኘሁ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ አንድ ነገር
አደርጋለሁ፤ከኋላዬ ያለውን ነገር እየረሳሁ
ከፊት ለፊቴ ያለውን ነገር ብቻ እመለከታ
ለሁ። [14]እግዚአብሔር በክርስቶስ ሊሰጠን
በሰማይ ያዘጋጀውን ሽልማት ለመቀበል ፥
ሩጫዬን ከግቡ ለማድረስ ጥረቴን እጥፍ
ድርብ አደርጋለሁ።
[15]እኛ በመንፈሳዊ ሕይወታችን የበሰልን
ክርስቲያኖች ፥ ስለዚህ ነገር አንድ ዓይነት
አስተሳሰብ እንደሚኖረን ተስፋ አደርጋ
ለሁ። ምናልባት ከዚህ የተለየ አሳብ ያላች
ሁም ብትኖሩ እግዚአብሔር እውነቱን እን
ደሚገልጽላችሁ አምናለሁ። [16]እንግዲህ
እስከ አሁን ያወቅነውን እውነት እንደያዝን
በዚያው ጸንተን እንኑር።
[17]ወንድሞች ሆይ ፥ በሕይወታችሁ የእ
ኔን አርአያ ተከተሉ። የእኔን አርአያነትም
ማን እንደሚከተል ልብ ብላችሁ አስተ
ውሉ። [18]ከዚህ በፊት ደጋግሜ እንደ ነገር
ኳችሁ ፥ አሁንም እያለቀስኩ እነግራችኋ
ለሁ። የክርስቶስ የመስቀሉ ጠላቶች ሆነው
ሳሉ፥ 'ክርስቲያን ነን' እያሉ የሚያስመስሉ
ብዙ ሰዎች አሉ። [19]የእነርሱ መጨረሻ የዘ
ላለም ጥፋት ነው። ምክንያቱም አምላካ
ቸው ሆዳቸው ነውና። እነዚህ ሰዎች አስ
ከፊ የሆነ ነገር ሲፈጽሙ እንኳን፥በማፈር
ፈንታ ይኩራሩበታል። የሚያስቡትና የሚጨ
ነቁት ምድራዊ ስለሆነው ሕይወት ብቻ
ነው። [20]እኛ ግን አገራችን ክርስቶስ በሚገ
ኝበት በሰማይ ነው። ታዳጊያችን ክርስቶ
ስም ከዚያ ተመልሶ የሚመጣበትን ቀን በና
ፍቆት እንጠባበቃለን። [21]እርሱ ሲመጣም
ይህንን በስባሽና ፈራሽ የሆነውን ሥጋችንን
ይለውጣል። ሁሉን ነገር በሚገዛበት
ኃይሉ ፥ የእኛንም አካል ልክ እንደ እርሱ
አካል እንዲከብር ያደርገዋል።

## ምዕራፍ 4

[1]የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ ክርስቲ
ያን ወንድሞቼ ሆይ ፥ እናንተ ደስታዬና
ከጌታ የምቀበለው ሽልማት ምክንያቶች
ናችሁ። እንግዲህ ለጌታ ታማኝ በመሆን
ጸንታችሁ ኑሩ።
[2]እነዚያን የተጣሉትን ሁለት እኅቶች፥
ኤዎድያንንና ሲንጤኪን ተስማምተው እን
ዲኖሩ በጌታ እመክራቸዋለሁ። መጣላታቸ
ውን ትተው በሰላምና በፍቅር ሊኖሩ ይገ
ባል። [3]አንተም በወንጌል የሥራ ባልደረ
ባዬ፥እነዚህን እኅቶች እንድታስታርቅና እን
ድታስማማ አሳስብሃለሁ። እነዚህ እኅቶች
ከእኔ ፥ ከቀሌምንጦስና ስማቸው በሕይወት
መጽሐፍ ከተጻፈው አገልጋዮች ጋር
ሆነው ፥ ወንጌልን ለሰዎች ለማዳረስ ብዙ
ደክመዋል።
[4]ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ። ደግ
ሜም እላለሁ ደስ ይበላችሁ። [5]ገርነታችሁ

ለሰው ሁሉ ግልጽ ይሁን። ጌታ ቅርብ
ነው። [6]ስለ ምንም ነገር ቢሆን ከማሰብና
ከመጨነቅ ይልቅ፥በጸሎትና በልመና ፍላጎ
ታችሁን ለእግዚአብሔር ንገሩት። ምስጋ
ናም መስጠት አትርሱ። [7]አእምሮ ሊያስተ
ውለው ከሚችለው በላይ የሆነው የእግዚአ
ብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በኢየ
ሱስ ክርስቶስ በጸጥታ ይጠብቃል።

[8]በመጨረሻም አንድ ነገር ልነግራችሁ
እፈልጋለሁ። አሳባችሁን እውነተኛ፥ክቡር፥
ትክክለኛ፥ንጹሕና ተወዳጅ በሆነ ነገር ላይ
አውሉት። እግዚአብሔርን ለማመስገኛ ምክ
ንያት የሚሆኑ ነገሮችን አእምሮአችሁ ያው
ጠንጥን። በእነርሱም ደስ ይበላችሁ። [9]እኔ
ሳደርግ ያያችሁትንና የተማራችሁትን ነገ
ሮች ብታደርጉ የሰላም አምላክ ከእናንተ
ጋር ይሆናል።

[10]እንደገና እኔን ለመርዳት በማሰባችሁ
በጣም አመሰግናችኋለሁ። ጌታንም ስለዚህ
በጣም አመሰግነዋለሁ። ከዚህ በፊትም
ቢሆን በሚቻላችሁ ሁሉ ያለመሰልቸት
ልትረዱኝ ጥረት እንዳደረጋችሁ አውቃ
ለሁ። [11]ይህን ሁሉ የምለው ችግር ስላለ
ብኝ አይደለም። ምክንያቱም ማጣትንም
ሆነ ማግኘትን ተምሬአለሁ።

[12]አጥቶ መቸገርንም ሆነ አግኝቶ መክበ
ርን አይቻለሁ። 'ያለኝ ይበቃኛል' ብሎ፥
ረክቶ የመኖርን ምሥጢር አውቄአለሁ።
መራብንም፥ መጥገብንም ቀምሻለሁ።
[13]ጌታ እንዳደርገው የሚፈልገውን ነገር
ሁሉ፥ኃይልና ብርታት በሚሰጠኝ በክርስ
ቶስ እፈጽመዋለሁ። [14]ሆኖም በዚህ በች
ግሬ ጊዜ እኔን ለመርዳት ማሰባችሁ ተገቢ
ነገር ነው።

[15]እንደምታስታውሱት ሁሉ፥በመጀመ
ሪያ የምሥራቹን ቃል ለማስተማር ከመቄዶ
ንያ በተነሣሁ ጊዜ፥ከእናንተ በቀር በጉዞዬ
የረዳኝ ሌላ ቤተክርስቲያን አልነበረም።
እናንተ ለጉዞዬ የሚያስፈልገኝን ነገር በመ
ስጠትም ሆነ በማስተናገድ ብዙ ረድታችሁ
ኛል። [16]በተሰሎንቄ በነበርኩበት ጊዜ
እንኳ ሁለት ጊዜ የላካችሁልኝ እርዳታ
ደርሶኛል። [17]ይህንን ስል አሳቤን ሁሉ በስ
ጦታው ላይ መጣሌ አይደለም። ስለ ዋላች
ሁልኝ ውለታ የምታገኙትን ዋጋ እያሰብኩ
ደስ እንደሚለኝ ለመግለጽ ነው።

[18]አሁንስ ምንም የሚጐድለኝ ነገር
የለም። ምክንያቱም አፍሮዲጡ ሲመጣ፥
መዓዛው እንደ ሽቱ የሚሸተውንና ጌታን
የሚያስደስተውን ስጦታችሁን ይዞልኝ መጥ
ቷል። [19]አምላኬ ከከበረው ባለጠግነቱ፥በክ
ርስቶስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሰጣች
ኋል። [20]አምላካችንና አባታችን ለሆነው
ለእግዚአብሔር፥እስከ ዘላለም ድረስ ክብር
ይሁን፤አሜን።

[21]ለክርስቲያኖች ሁሉ የከበረ ሰላምታ
ዬን አቅርቡልኝ። ከእኔ ጋር ያሉት ወንድ
ሞችም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። [22]ቅዱ
ሳን ሁሉ፥በተለይም በቄሣር ቤተ መንግ
ሥት ውስጥ ያሉት ክርስቲያኖች ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል።

[23]የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በረከት
ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን፤አሜን።

የናንተው
ጳውሎስ

# ሐዋርያው ጳውሎስ
# ለቈላስይስ ሰዎች የጻፈው መልእክት

## መግቢያ

የዚህ መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈበት ዘመን ግን በውል ተለይቶ አልታወቀም። ይሁን እንጂ በ58 እና በ64 ዓ.ም. መካከል ካሉት ዓመታት ባንዱ መሆኑ ይገመታል። የመልእክቱ ዓላማ የክርስቶስን ታላቅነትና የቈላስይስ ሰዎች የተቀበሉትን ጸጋ ለመግለጽ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ፥ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ማለት የተቀደሰ እውነተኛ ደስታ የሞላበት ሕይወት ሊገኝ የሚችለው፥ ክርስቶስን በማመን ብቻ መሆኑን ምዕመናንን አበክሮ ያሳስባቸዋል። የሰው አእምሮ የተራቀቀበት ፍልስፍናና አጉል የአምልኮ ሥርዓት፥ከንቱና አደገኛ መሆኑንም ጨምሮ ያስገነዝባቸዋል።

---

## ምዕራፍ 1

1 የክርስቶስ መልእክተኛ እንዲሆን እግ
ዚአብሔር ከመረጠው ከጳውሎስና ከወን
ድም ጢሞቴዎስ የተላከ።
2 በክርስቶስ ወንድሞቻችን ለሆናችሁት
በቈላስይስ ከተማ ለምትኖሩ ታማኝና ቅዱ
ሳን ክርስቲያኖች፥ እግዚአብሔር አባታችን
ጸጋውንና ሰላሙን እንዲያበዛላችሁ እንመኝ
ላችኋለን።
3 ስለ እናንተ በጸለይን ቍጥር እግዚአብ
ሔርን እናመሰግናለን። 4 ምክንያቱም በእግ
ዚአብሔር ላይ ያላችሁ እምነት የጠነከረ፥
ለክርስቲያኖችም የምታሳዩት ፍቅርም ከፍ
ያለ መሆኑን በመስማታችን ነው። 5 ወንጌ
ልን ከሰበክንላችሁ ከመጀመሪያው ጊዜ አን
ሥቶ እስከ አሁን ድረስ፥በሰማይ የተዘጋጀላ
ችሁን ደስታ በናፍቆት እንደምትጠባበቁ
እናውቃለን። 6 ለእናንተ የተሰበከላችሁና
የእግዚአብሔርን ጸጋ በእውነት የተረዳችሁ
በት ወንጌል፥እነሆ ዛሬም በመላው ዓለም
እየተሰበከ፥የሰዎችንም ሕይወት በመለወጥ
ላይ ይገኛል።
7 ታማኝ የክርስቶስ አገልጋይ የሆነውና
እጅግ የምናፈቅረው የሥራ ባልደረባችን
ኤጳፍራ፥በእኛ ምትክ የወንጌልን ቃል እን
ደሰበከላችሁ እናስታውሳለን። 8 መንፈስ
ቅዱስ ሰዎችን ማፍቀር እንድትችሉ ጸጋ
ውን እንደ ሰጣችሁ ኤጳፍራ ነግሮናል።
9 ስለዚህ ይህን ከሰማንበት ጊዜ ጀምሮ፥እግ
ዚአብሔር ፈቃዱ ምን እንደሆነ እንዲገል
ጽላችሁና፥መንፈሳዊ ዕውቀትና ጥበብ እን
ዲሰጣችሁ ከመጸለይ ተቆጥበን አናውቅም።
10 እግዚአብሔር ከእናንተ የሚጠብቀውንና
ደስ የሚሰኝበትን ኑሮ በመኖር የመልካም
ሥራን ፍሬ እንድታሳዩ፥ ስለ እግዚአብሔ
ርም ባላችሁ ዕውቀት እየበሰላችሁ እንድት
ሄዱ እንጸልይላችኋለን።
11 እንደዚሁም ደግሞ እግዚአብሔር በታ
ላቅ ኃይሉ እንዲያበረታችሁ፥በማንኛውም
ጊዜ ጠንካራ ሆናችሁና በጌታ ደስታ ተሞ
ልታችሁ እንድትገኙ እንጸልያለን። 12 ብር
ሃን በሆነው መንግሥቱ የሚገኘውን በረከት
ሁሉ ለመካፈል ብቁ ያደረጋችሁ እግዚአብ
ሔር ምስጋና ይግባው። 13 ምክንያቱም
እርሱ ከሰይጣን ተገዢነትና ከጨለማ መንግ
ሥቱ አውጥቶ፥ ብርሃን ወደሆነው ውድ
ልጁ መንግሥት እንድንገባ አድርጎናል።
14 ልጁም ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ነጻ
አውጥቶ ኃጢአታችንን ይቅር ብሎልናል።
15 በዓይን የማይታየው እግዚአብሔር
አምሳያ፥ክርስቶስ ራሱ ነው። እርሱም ማን
ኛውም ነገር ከመፈጠሩ በፊት የነበረና የፍ
ጥረት ሁሉ በላይ የሆነ፥የእግዚአብሔር የበ
ኩር ልጁ ነው። 16 በዓይን የሚታዩና የማይ
ታዩ፥በሰማይና በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ፤
ዙፋኖች፥ ኃይሎች፥ ገዢዎችና ሥልጣኖች
በእርሱና ለእርሱ ተፈጥረዋል። 17 እርሱ
ከሁሉም ነገር በፊት ነበር። ሁሉንም ነገር
በአንድነት ያያያዘ እርሱ ነው። 18 እርሱ
የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። ቤተ ክርስቲያ
ንም የተገነባችው የእርሱ አካል በሆኑት
አማኞች ነው። እርሱ ከሁሉ ቀዳሚና
ከሞት በመነሣትም የሁሉ መጀመሪያ
ነው። 19 ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው፥እግዚአ
ብሔር የሙላቱ ፍጹምነት በልጁ በክርስ

ቶስ እንዲገለጽ በመፍቀዱ ነው።
20 አንድ ልጁ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው
ደም እግዚአብሔር ሰላምን በሰማይና በም
ድር ላይ መሥርቶ ሁሉ ነገር እንደገና
ከራሱ ጋር እንዲታረቅ አደረገ። 21 ከዚህ
በፊት ከእግዚአብሔር ርቃችሁ የምትኖሩና
በክፉ አስተሳሰባችሁና ሥራችሁ ምክንያት
ጠላቶቹ ነበራችሁ። 22 አሁን ግን ልጁ
በሥጋ ተገልጹ በመስቀል ላይ በመሞቱ፥
ወዳጆቹ እንድትሆኑና በፊቱም ያለ ምንም
ነቀፋ ለመቆም እንድትችሉ አበቃችሁ።
23 አሁን ከእናንተ የሚጠበቀው ቃሉን ተቀ
ብላችሁ እንድታምኑና በእምነታችሁ ጸንታ
ችሁና ጠንክራችሁ እንድትቆሙ ነው።
ይህም ለእናንተ የተሰበከው የወንጌል ቃል
አሁንም በዓለም ዙሪያ ሁሉ በመሰራጨት
ላይ ነው። እኔ ጳውሎስም ይህንን የምሥ
ራች ቃል ለሰዎች የመናገር ዕድል ስላገ
ኘሁ ደስ ይለኛል።
24 ስለ እናንተ በምቀበለው መከራ ደስ
ተኛ ነኝ። ምክንያቱም ክርስቶስ አካሉ ስለ
ሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከተቀበለው
መከራ የቀረውን ዕድል እግኝቻለሁና።
25 ከእግዚአብሔር ቃል ምንም ሳላስቀር
እንድሰብክላችሁ እግዚአብሔር የቤቱ ክርስ
ቲያን አገልጋይ አድርጎ ወደ እናንተ ልኮ
ኛል። 26-27 ለብዙ ዘመናት እግዚአብሔር
ይህንን ምሥጢር አድርጎ ይዞት ነበር።
አሁን ግን ለሚወዱትና ለሚያምኑት ሁሉ
ግልጽ አደረገው። በዚህ ምሥጢር መገለጽ
ምክንያት የሚገኘው ክብርና ብልጽግና፥
ለአሕዛብም ሁሉ እንዲሆን እግዚአብሔር
ወሰነ። ይህም ምሥጢር፥ በልባችሁ ያለው
ክርስቶስ ተወዳዳሪ የሌለው የክብር ተስፋ
መሆኑን ያበሥራል።
28 ስለዚህ በደረስንበት ሁሉ ለሚሰሙን
ስለ ክርስቶስ እንናገራለን። በዚህም በተሰ
ጠን ጥበብ ሰዎችን እያስተማርን፥በክርስቶስ
ፍጹማን ሆነው እንዲገኙ ለማድረግ እንተጋ
ለን። 29 ይህን እንዳደርግ እግዚአብሔር ኃላ
ፊነት ሰጥቶኛል። ይህንን የተሰጠኝን ኃላፊ
ነት ያለ ፍርሃት ከግቡ አደርሳለሁ የምለ
ውም፥ የጌታ ኃይል በእኔ ውስጥ በመኖሩ
ብቻ ነው።

## ምዕራፍ 2

1 ለእናንተና በሎዶቅያ ላለችው ቤተ
ክርስቲያን እንዲሁም በግል ለማያውቁኝ
ወገኖች ሁሉ፤ ምን ያህል በጸሎት እየታገ
ልኩ መሆኔን ብታውቁ ደስ ባለኝ። 2 ስለ
እናንተ የምጸልየውም፥ ብርታት አግኝታ
ችሁ እርስ በእርሳችሁ በጽኑ ፍቅር እንድት
ተሳሰሩና፥እግዚአብሔር ለሰዎች የገለጸውን
ምሥጢር ክርስቶስን ራሱን፥በሚገባ እንድ
ታውቁ ነው። 3 ገና ምንም ያልተነካለት
የጥበብና የዕውቀት ሀብት በክርስቶስ ውስጥ
ተሠውሮ ይገኛል።
4 ስለዚህ ጉዳይ ልነግራችሁ የፈለግሁ
በት ምክንያት፥ምናልባት አንዳንድ ሰዎች
በለስላሳ አንደበታቸው እንዳያታልሏችሁ
ስለ ፈራሁ ነው። 5 ምንም እንኳ በአካል
አብሬአችሁ ባልሆንም ልቤ ግን ከእናን
ተው ጋር ነው። በእምነታችሁ ጸንታችሁ
በመቆማችሁም ከልክ ያለፈ ደስታ ይሰማ
ኛል። 6 ክርስቶስ ሊያድናችሁ የሚችል
መሆኑን አውቃችሁ እንዳመናችሁት ሁሉ፥
አሁንም ዕለት በዕለት ከእርሱ ጋር ያላችሁ
ኑሮ የጸና ይሁን። 7 ስለዚህ በእርሱ ላይ
ተመሥርታችሁና ሥር ሰድዳችሁ፥ለመንፈ
ሳዊ ሕይወታችሁ የሚያስፈልጋችሁን
ምግብ ከእርሱ እየተቀበላችሁ፥የተማራችሁ
ትን እውነተኛ ትምህርት አጥብቃችሁ
ያዙ። ሕይወታችሁም ጌታ ካደረገላችሁ
በጎ ነገር የተነሣ በደስታና በምስጋና የተ
ሞላ ይሁን።
8 ይህን የመሰለውን እምነታችሁንና ደስ
ታችሁን፥አንዳንድ ሰዎች መርዝ በሆነ ፍል
ስፍናቸው እንዳይበክሉባችሁ ተጠንቀቁ።
የእነርሱ አሳብ የተመሠረተው ስለክርስቶስ
በተሰጠው ትምህርት ላይ ሳይሆን፥ሰው
ሠራሽ በሆነ የዚህ ዓለም ፍልስፍናና የሰ
ዎች ልማድ ላይ ነው። 9 የእግዚአብሔር
መለኮታዊ ባሕርይ በሙሉ፥በሥጋ በክርስ
ቶስ ተገልጦ ይኖራል። 10 ስለዚህ ክርስቶስን
የሕይወታችሁ ገዢ አድርጋችሁ በተቀበላች
ሁት ጊዜ፥ከእርሱ ጋር ካላችሁ ሕብረት
የተነሣ፥የሕይወትን ሙላትና ፍጹምነት
ተቀዳጅታችኋል። እርሱ የሥልጣንና የኃ
ይል ሁሉ ራስ ነው።
11 ወደ ክርስቶስ በተመለሳችሁ ጊዜ
ከክፉ ፍላጎታችሁና ምኞታችሁ ነጻ እንድ
ትሆኑ፥ሥጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ የሆነ
የልብ መገረዝ ተገርዛችኋል። 12 በተጠመቃ
ችሁበትም ጊዜ ክፉ የሆነው አሮጌ ተፈጥሮ
አችሁ፥ከክርስቶስ ጋር አብሮ ተቀብሮአል።
እንደዚሁም ደግሞ ክርስቶስን ከሞት ባስነ
ሣው በእግዚአብሔር ኃይል ስላመናችሁ
ከእርሱ ጋር ተነሥታችኋል።
13 ከዚህ ቀደም በበደላችሁና በኃጢአ
ተኛ ተፈጥሮአችሁ ምክንያት ሙታን ነበራ

ችሁ፤ አሁን ግን እግዚአብሔር ኃጢአታች
ሁን ይቅር በማለቱ የክርስቶስን ሕይወት
አግኝታችሁ በነፃነት ለመመላለስ በቅታች
ኋል። 14ክርስቶስ በሕግ ፊት መክፈል የነበ
ረብንን ዕዳና የተቃወሞ ክስ በሙሉ ሰርዞ
በመስቀልም ላይ ቸንክሮ ይቅርታን አስገኘ
ልን። 15በዚህ ዓይነት የሰይጣንን ኃይልና
ሥልጣን ሽሮ በመስቀል ላይ የተገኘውን
ድል፣ ዓለም ሁሉ በይፋ እንዲያውቀው አደ
ረገ።

16ስለዚህ በምትበሉትና በምትጠጡት
ነገር ምክንያት፣ ወይም ሰንበትን፣ በዓላትንና
የወር መግቢያ የሆነውን ቀን አላከበራች
ሁም በማለት፣ ማንም ሰው ሊወቅሳችሁ አይ
ገባም። 17እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሊመጣ ያለ
ውን ነገር የሚያመለክቱ ጊዜያዊና ኃላፊ
ምስሎች ነበሩ። ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ግን
ፍጻሜ አግኝተዋል። 18ማንም ሰው መላእክ
ትን ካላመለካችሁ እያለ በሐሰት ትሕትና
ቀርቦ ከእምነታችሁ አሰናክሎ ሽልማታች
ሁን እንዳያሳጣችሁ ተጠንቀቁ። እንዲህ
ዓይነቱ ሰው ራዕይ አየሁ በማለት በከንቱ
የሚታበይና ትሑት መስሎ መታየት የሚ
ወድ ትዕቢተኛ ሰው ነው። 19ይህን ማለት
የሚደፍር ሰው፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ ከሆ
ነው ከክርስቶስ ጋር ግንኙነት የለውም
ማለት ይቻላል። እኛ ግን በክርስቶስ እርስ
በእርስ ተሳስረን ከእርሱ የምናገኘውንም
መንፈሳዊ ምግብ እየተመገብን እግዚአብ
ሔር ወዳቀደልን ፍጹምነት እናመራለን።

20ከክርስቶስ ጋር ስለ ሞታችሁና ከዓለ
ምም አስተሳሰብ ስለራቃችሁ፣ ዓለማዊ የሆነ
መመሪያ እንዴት ትከተላላችሁ? 21በተለ
ይም፣ «ይህንን አትብሉ፣ ያንን አትቅመሱ!
ይህንን ደግሞ በእጃችሁ እንኳን አትንኩ»
የሚለውን ሰው ሠራሽ ሕግ አትከተሉ።
22እነዚህ ሕጎች የተመሠረቱት በሰው ሥር
ዓትና ትምህርት ላይ ስለሆነ፣ በሥራ ላይ
ከዋሉ በኋላ ይጠፋሉ። 23በገዛ ፈቃድ በሚ
ደረግ አምልኮ፣ በከንቱ ትሕትናና ሰውነትን
በማጕሳቈል የተመሠረቱት እነዚህ ሰው
ሠራሽ ሥርዓቶች የጥበብ መልክ አላቸው።
ነገር ግን፣ ሰው በራሱ ሥራ እንዲኩራራ
ከማድረግ በቀር፣ የሰውን ክፉ ምኞትና
ከንቱ አስተሳሰብ በመለወጥ ረገድ ምንም
ጥቅም አይሰጡም።

## ምዕራፍ 3

1ከክርስቶስ ጋር ከሞት ከተነሣችሁ፣ ልባ
ችሁና አሳባችሁ እርሱ በክብርና በኃይል
ከእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በሰ
ማይ ይሁን። 2አእምሮአችሁን በላይ በሰ
ማይ በሚገኙ ነገሮች ላይ አድርጉ እንጂ፣
በዚህ ምድር ላይ ስላሉት ነገሮች በማሰብ
አታስጨንቁት። 3የሞተ ሰው ከዚህ ዓለም
ነገር እንደሚለይ ሁሉ፣ እናንተም ስለዚህ
ዓለም ጉዳይ አትጨነቁ። ምክንያቱም እው
ነተኛው ሕይወታችሁ ያለው፣ በላይ በሰማይ
ከክርስቶስ ጋር ነውና። 4ሕይወታችን የሆ
ነው ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፣ እኛም ከእ
ርሱ ጋር አብረን እንገለጣለን። የክብሩ ተካ
ፋዮችም እንሆናለን።

5ስለዚህ በምድር ላይ ያሉትን ክፉ
ምኞቶቻችሁን ሁሉ አስወግዱ። ከዝሙት፣
ከርኩሰትና ከክፉ ምኞት ጋር፣ ምንም ዓይ
ነት ግንኙነት አይኑራችሁ። መጐምጀትም
ጣዖትን እንደማምለክ ነውና ከእርሱም
ራቁ። 6እነዚህን ነገሮች ማድረግን በሚያዘ
ወትሩ ሰዎች ላይ፣ አስፈሪ የሆነው የእግዚአ
ብሔር ቁጣ ይደርስባቸዋል። 7ክርስቶስን
ከማወቃችሁ በፊት እናንተ እነዚህን ነገሮች
ታደርጉ ነበር። 8ነገር ግን አሁን ይህን የመ
ሰለውን የቁጣ፣ የርግማን፣ የስድብና የጸያፍ
ንግግር ልማድ ከአሳባችሁ ማስወገድ አለባ
ችሁ።

9ክርስቶስን ከማወቃችሁ በፊት ሕይወ
ታችሁ የውሸት ማኅደር ነበር። አሁን ግን
ያን አሮጌውን ሕይወት አስወግዳችሁ ከጌታ
አዲስ ሕይወት ስለተቀበላችሁ፣ እርስ በእርሳ
ችሁ ውሸት አትነጋገሩ። 10ይህም አዲስ
ሕይወት የፈጠረውን ክርስቶስን ለመምሰል
ዘወትር በእርሱ እውቀት እየታደሰ የሚሄድ
ነው። 11በክርስቶስ በተገኘው አዲስ ሕይ
ወት የአንድ ሰው ዘሩ ወይም ዜግነቱ፣ መገ
ረዙ ወይም አለመገረዙ፣ መማሩ ወይም አለ
መማሩ፣ ገዢነቱ ወይም ተገዢነቱ፣ ቅድሚያ
የሚሰጠው ነገር አይደለም። ምክንያቱም
ክርስቶስ የሁሉም ነው አምነው በተቀበሉ
ትም ሁሉ ውስጥ ይኖራል።

12ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ወደዳች
ሁና ለዚህ ቅዱስ ሕይወት ስለመረጣችሁ፣
እናንተም ደግሞ ርኅሩሆች፣ ምሕረት ወዳ
ጆች፣ ትሑቶች፣ የዋሆችና ትዕግሥተኞች
እንድትሆኑ ያሻል። 13ከዚህም በቀር እርስ
በእርስ ለመቻቻልና ይቅርም ለመባባል
የተዘጋጃችሁ ሁኑ። በማንም ሰው ላይ
ቂም አትያዙ። ክርስቶስ እናንተን ይቅር
እንዳላችሁ እርስ በእርሳችሁ ይቅር ተባ
ባሉ።

14ከእነዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ፣ ፍጹም

በሆነ አንድነት የሚያስተሳስረውን ፍቅርን
ልበሱ። 15 ልባችሁንና አእምሮአችሁን የክ
ርስቶስ ሰላም ሁልጊዜ ይግዛው። እንደ
አንድ አካል ክፍሎች ለሰላም ተጠርታችኋ
ልና። ሁልጊዜም አመስግኑ።
16 ጥበብ በተሞላው መንገድ አንዱ ሌላ
ውን ያስተምር፥ ይምከርም። በመዝሙርና
በውዳሴ፥ በመንፈሳዊ ቅኔም ከልብ የሆነ
ምስጋና ለእግዚአብሔር አቅርቡ። 17 የምታ
ደርጉትንና የምትናገሩትን ሁሉ፥በጌታ በኢ
የሱስ ክርስቶስ ስም አድርጉት በክርስቶስም
ለእግዚአብሔር ምስጋና ለመስጠት ወደ
ዙፋኑ ቅረቡ።
18 ሚስቶች ሆይ፥የጌታ እንደመሆናችሁ
መጠን ክርስቲያናዊ ተግባራችሁ ነውና ለባ
ሎቻችሁ በፍቅር ታዘዙ። 19 ባሎች ሆይ፥
እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ። እንደዚ
ሁም ለሚስቶቻችሁ ደጎችና ገሮች እንጂ፥
ክፉና መራራ አትሁኑባቸው።
20 ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በሁሉ
ነገር የምትታዘዙ ብትሆኑ፥እግዚአብሔርን
ታስደስቱታላችሁ። 21 አባቶች ሆይ፥ ልጆቻ
ችሁ ተበሳጭተው ተስፋ እንዳይቆርጡ፥
በቁጣ አታስመርሯቸው።
22 አገልጋዮች ሆይ፥ አዩኝ አላዩኝ በማ
ለት ለመወደድ ሳይሆን፥ምድራዊ አሳዳሪዎ
ቻችሁን በቅንነት አገልግሉ። ክርስቲያን
ስለ ሆናችሁና ክርስቶስንም ስለምትፈሩ፥
በደስታ ታዘዙላቸው። 23 ሰውን ሳይሆን
ጌታን እንደምታገለግሉ በመቁጠር፥የተሰጣ
ችሁን ሥራ በትጋት ፈጽሙ። 24 የምታገለ
ግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና የሚገባችሁን
ዋጋ ራሱ እንደሚከፍላችሁ ታውቃላችሁ።
25 የሚጠበቅባችሁን ሳትፈጽሙ ብትገኙ
ግን፥ተገቢውን ቅጣት ጌታ እንደሚሰጣችሁ
አትዘንጉ። በእርሱ ዘንድ አድልዎ የሚባል
ነገር የለምና።

## ምዕራፍ 4

1 አሳዳሪዎች ሆይ፥እናንተም የምታደር
ጉትን ሁሉ ከሰማይ የሚመለከት ጌታ እን
ዳለ በማወቅ፥ለአገልጋዮቻችሁ መልካምና
ደግ ሁኑላቸው።
2 በንቃትና በምስጋና በተሞላ ልብ በጸ
ሎት የምትተጉ ሁኑ። 3 የታሠርኩበትን የክ
ርስቶስን ወንጌል በይፋ እንድናውቅ መልእ
ክቱንም ለማስተላለፍ የምንችልበትን በር
እግዚአብሔር እንዲከፍትልንም ስለእኛ
ጸልዩ። 4 ይህንን የወንጌል ቃል፥ያለ ምንም
ፍርሃትና ምንም ነገር ሳላስቀር በግልጽ
መስበክ እንድችል፥ እኔንም በጸሎታችሁ
አስታውሱኝ።
5 ወንጌልን ለመስበክ የሚያጋጥሙአች
ሁን ዕድሎች ሁሉ ተጠቀሙባቸው። ከማያ
ምኑ ሰዎች ጋር ያላችሁ ግንኙነት ሁሉ፥
በማስተዋልና በጥንቃቄ ይሁን። 6 ንግግራ
ችሁ ሁሉ ቁም ነገርና ጸጋ የተሞላበት
ይሁን። ለሰው ሁሉ ተገቢ የሆነውን የጨዋ
ሰው መልስ ስጡ።
7 ተወዳጅ የሆነው ወንድማችን ቲኪ
ቆስ፥ስለ እኔ ሁሉንም ነገር በሰፊው ያጫው
ታችኋል። እርሱ እዚህ ከእኔ ጋር ሆኖ
ጌታን ያገለገለ ታማኝ ወንድም ነው። 8 እን
ዴት እንዳላችሁ እንዲያይ፥እንዲያጽናናች
ሁና እንዲያበረታታችሁ ወደ እናንተ ልኬ
ዋለሁ። 9 እንደዚሁም ያገራችሁ ሰው የሆነ
ውን፥ታማኝና ተወዳጅ ወንድማችንን አናሲ
ሞስን፥ከእርሱ ጋር ልኬዋለሁ። ስለዚህ ከሁ
ለቱ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ መረዳት
ትችላላችሁ።
10 ከእኔ ጋር በእሥር ቤት ታሥሮ የሚ
ገኘው አርስጥሮኮስ፥ሰላምታውን ያቀርብላ
ችኋል። ከዚህ በፊት እንደ ነገርኳችሁ
ሁሉ፥ ምናልባት ማርቆስ ወደ እናንተ
የመጣ እንደሆነ፥ልባዊ አቀባበል አድርጉ
ለት። 11 ኢዮስጦስ በመባል የሚታወቀው
ኢያሱ ሰላምታ ያቀርብላችኋል። ለጊዜው
ከጎኔ ሳይለዩ የእግዚአብሔርን መንግሥት
በማገልገል ላይ ያሉት አይሁድ ክርስቲያ
ኖች፥እነዚህ ብቻ ናቸው። እነዚህ ወንድ
ሞች ምን ያህል እንዳጽናኑኝ የማውቀው
እኔ ራሴ ብቻ ነኝ።
12 የእናንተ አገር ሰው የሆነው የኢየሱስ
ክርስቶስ አገልጋይ ኤጳፍራም፥ የናፍቆት
ሰላምታውን ያቀርብላችኋል። ኤጳፍራ እግ
ዚአብሔር እንዲያበረታችሁና ፈቃዱንም
እንዲገልጽላችሁ፥ ሁልጊዜ ባለማቋረጥ ስለ
እናንተ በመጸለይ ላይ ይገኛል። 13 ስለ እና
ንተ ብቻም ሳይሆን፥በሎዶቅያና በኢያራ
ከተማ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ፥በጸሎት
በመታገል ላይ እንደሆነ ላረጋግጥላችሁ
እወዳለሁ።
14 ወዳጃችን ሐኪሙ ሉቃስና ዴማስም፥
ሰላምታቸውን ያቀርቡላችኋል።
15 እናንተም በሎዶቅያ ከተማ ላሉት
ክርስቲያኖችና ለንምፋ፥ እንዲሁም በቤቷ
ውስጥ ለጸሎትና ለአምልኮ ለሚሰበሰቡት
ክርስቲያኖች ሁሉ፥የከበረ ሰላምታዬን አቅ
ርቡልኝ። 16 ይህን መልእክት ካነበባችሁ
በኋላ፥በሎዶቅያ ከተማ ላለችው ቤተ ክርስ

ቲያን አስተላልፉልኝ። ለእነርሱ የጻፍ
ኩትንም መልእክት ተቀብላችሁ አንብቡ።
17 አክሪጳን ፥ «እግዚአብሔር ያዘዘህን ነገር
ሁሉ በጥንቃቄ ከመፈጸም እንዳትቦዝን»
በሉልኝ።
18 ይህ ሰላምታ እኔ ራሴ በገዛ እጄ የጻፍ
ኩት ነው። እሥር ቤት ውስጥ ያለሁትን
እኔን ወንድማችሁን በጸሎታችሁ አስታው
ሱኝ።

የጌታ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

ጳውሎስ